# የ10 ቀናት የጸሎት ቆይታ

**1ኛ ቀን**

**እጅግ ክቡር የሆነው የየሱስ ስጦታ**

{...በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?›› ሉቃስ 11፡13

**አንዳች የለኝም**

‹‹ጌታ ሆይ፤ ጸሎትን አስተምረን!›› በማለት ነበር ደቀ መዛሙርቱ ልመና ያቀረቡት፡፡ የሱስ በየእለቱ ከሰማይ አባቱ ጋር ምን ያህል ሕብረት ያደርግ እንደነበረ በማየታቸው በእነሱም ሕይወት ያው ኃይል እንዲገለጥ ተመኙ፡፡

የሱስ ለልመናቸው ምላሽ የሰጠው በሦስት ክፍሎች የተከፈለ የማይዘነጋ የጸሎት ትምህርት በማቅረብ ነበር፡፡ ሦስቱ ክፍሎች የጌታ ጸሎት፣ በእኩለ ሌሊት ወደ ጓደኛ ቤት የሄደው ሰው ምሳሌያዊ ታሪክ፣ እና በዋና መደምደሚያነት የተሰጠው በቀጣይነት ስለመንፈስ ቅዱስ መለመን አስፈላጊ የሞሆኑ ማሳሰቢያ ናቸው፡፡ (ሉቃስ 11፡1-13)

ምሳሌያዊው ታሪክ የሚናገረው እጅግ አምሽቶ ወደ ቤቱ የመጣውን እንግዳ የሚያስተናግድበት ምግብ ስላልነበረው ሰው ነው፡፡ ሰውየው በፍጥነት ወደ ጎረቤቱ ሄደ ‹‹አንዳች የለኝም›› በማለት ነበር ለእንግዳው የሚያቀርበው ዳቦ የለመነው፡፡ ለእንግዳው ማካፈል የሚችለው ዳቦ ማግኘት እስከቻለባት የመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስም ልመናውን ቀጥሎ ነበር፡፡ በዚህ ታሪክ የምናየው ለሰዎች የምናካፍለው ነገር ለማግኘት ወደ የሱስ መቅረብ እንደሚያስፈልገን ነው፡፡ የሕይወትን እንጀራ ለሰዎች ለማስተላለፍ በምናስብባቸው ብዙ ጊዜያት የምንገነዘበው የምንሰጠው አንዳች ነገር እንደሌለን ነው!

የሱስ ቀጥሎ ያደረገው በምሳሌያዊው ታሪክ የቀረበውን ችግር መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ልመና ማቅረብ አስፈላጊያችን ከመሆኑ እውነታ ጋር ማያያዝ ነበር፡፡ ‹‹እኔም እላችኋለሁ፡-... ለምኑ፣ ይሰጣችሁማል፤›› (ሉቃስ 11፡9)

**የሱስ በመጠየቅ ጽኑ በማለት ይጋብዘናል**

በሉቃስ 11 የምናየው የሱስ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን እንዲኖር መጠየቃችን ተገቢ ስለመሆኑ 10 ጊዜ አፅንዖት ሲሰጥ ነው፡፡ አንድን ነገር በልባችን እንድንይዝ ይህን ያህል ፍቅር በተሞላ ውትወታ እኛን ያሳሰበበት ሌላ ስፍራ አይታሰበኝም፡፡

‹‹እኔም እላችኋለሁ፡- ለምኑ፣ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፣ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል፡፡ የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል፡፡ አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ወይስ እንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?›› (ሉቃስ 11፡9-13)

የሱስ በእነዚህ ጥቂት ቁጥሮች ከመለመን ጋር ተያያዥነት ያላቸው ግሦችን 6 ጊዜ የተጠቀመ ሲሆን፣ 2 ጊዜ ከመፈለግ ጋር፣ 2 ጊዜም ከማንኳኳት ጋር በማያያዝ ሀሳቡን አጉልቶ አውጥቷል፡፡ እነዚህ ግሦች በሙሉ ድርጊትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እናም የሱስ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት እርምጃ መውሰድ እንዳለብን ነው በግልጽ ያሳየው፡፡ ስለመለመን ለመግለጽ መጨረሻ ላይ የተጠቀመበት የግሪክ ቃል ቀጣይነትን የሚያሳይ ሲሆን፣ አንዴ ብቻ ሳይሆን በቀጣይነት መጠየቅ እንደሚገባን የሚያስረዳ ነው፡፡ የሱስ ይህንን ልባዊ ግብዣ ያቀረበው መንፈስ ቅዱስን መሻት በውስጣችን እንዲ ነሳሳ ብሎ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስን የበለጸጉ በረከቶች በቀጣይነት የማንለምን ከሆነ፣ ወሳኝ የሆነ ነገር እንደሚያመልጠን ያውቃል፡፡

‹‹የክርስቶስ *መሠረታዊ ትምህርቶች*›› የሚል ትርጓሜ ባለው ‹‹Christ's Object Lessons›› የተሰኘ *መጽሐፍ እንዲህ* እናነባለን፡- ‹‹*እግዚአብሔር አንዴ ብቻ ጠይቃችሁ ትቀበላላችሁ አላለም፡፡ በመለመን እንድንጸና ነው አጥብቆ የሚያሳስበን፡፡ መጸለያችሁን ያለመታከት ቀጥሉ፡፡ በቀጣይነት መለመን ልመና የሚያቀርበውን ሰው የበለጠ ልባዊ የሚያደርገው ሲሆን፣ ልመና የሚያቀርብባቸውን ነገሮች ለመቀበል የበለጠ መሻት ያሳድርበታል፡፡* (p. 145)

የሱስ እራሱ በየእለቱ ረዘም ያለ የጸሎት ቆይታ ያደርግ የነበረው ለምን እንደሆነ እስቲ አሰብ አድርጉ፡፡ ኤለን ኋይት እንዲህ በማለት ታስረዳለች፡- ‹‹በየጠዋቱ ከሰማይ አባቱ ጋር በመነጋገር፣ በየእለቱ ከእሱ አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይቀበል ነበር››፡፡ (Signs of the Times, Nov. 21, 1895)

በዚህ ጉዳይ በእርግጥ የሱስ ምሳሌ ሆኖናል፡፡ እራሳችሁን እንዲህ በማለት ጠይቁ፡- ‹‹የሱስ በእየለቱ በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አስፈልጎት ከነበረ፣ ይህ ነገር ለእኔማ ምንኛ የበለጠ አስፈላጊ ነው?››፡፡

**ከቤተ ክርስቲያን አባል የተሰጠ ምስክርነት እና ማደፋፈሪያ**

*‹‹ላለፉት ሁለት ዓመታት የመንፈስ ቅዱስን መውረድ በሕይወቴ ለመለማመድ ስጸልይ ቆይቼ ነበር፡፡ … በውጤቱም ሊታመን በማይቻል ስምረት ከእግዚአብሔር ጋር ለመጓዝ በቅቻለሁ፡፡ የሱስን በውስጤ እንዲኖር፣ ፈቃዱን በእኔ እንዲያደርግ፣ እንዲሁም በየእለቱ በመንፈሱ እንዲያድሰኝ ከጠየቅሁት ወዲያ፣ በገላትያ 5 ያለው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወቴ ይበልጥ እውን እየሆነ መጥቷል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ እና ለሰዎች ስለ ክርስቶስ የመናገር ታላቅ ደስታ አድሮብኛል፤ ደግሞም ለሰዎች የመጸለይ ጠንካራ ፍላጎት ያለኝ ሆኛለሁ፡፡ በተጨማሪም፣ አኗኗሬ በድንቅ ሁኔታ ተቀይሯል፡፡ … ዛሬ የማደፋፍራችሁ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ለስድስት ተከታታይ ሳምንታት በየእለቱ እንድትጸልዩ እና የሚሆነውን እንድታዩ ነው፡፡››* (C.H.)

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

**ብዙ የጸሎት መልሶች የማናገኘው ለምንድን ነው?**

*‹‹… ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ ትለምናላችሁ፤ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም፡፡››* (ያዕቆብ 4፡2፣3)

*ውድ የሰማይ አባት ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በቀጣይነት መጸለይን ቻል ስላልን እባክህ ይቅር በለን፡፡ ሐጢአታችንን ስንናዘዝ ይቅር ስለምትለን እናመሰግንሃለን፡፡*

**ስለ መንፈስ ቅዱስ ልመና ማቅርባችን እግዚአብሔር ሊሰጠን የወደደውን ይህንን ስጦታ ምን ያህል ዋጋ እንደሰጠነው ያሳያል**

*‹‹እንኪያስ እናንተ ክፍዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?››* (ሉቃስ 11፡13)

*ውድ አባት ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስን ልትሰጠን ቃል ስለገባህ እናመሰግንሃለን፡፡ መንፈስ ቅዱስን አሁን እንድታወርድልን እንለምናለን፤ ጸሎታችንን ስለምትመልሰልንም እናመሰግንሃለን፡፡ በዚህ የተሰፋ ቃል መታመንን አስተምረን፡፡*

**እግዚአብሔር የተትረፈረፈ ሕይወት ሊሰጠን ይሻል!**

*‹‹በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኂ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ፡፡ ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤››* (ዮሐንስ 7፡38፣ 39)

*ውድ ጌታ ሆይ፤ በአንተ ለሚያምኑ ስለሰጠኸው የሕይወት ውኃ ወንዝ እናመሰግንሃለን፡፡ ይህንን የተስፋ ቃል በሕይወታችን ትፈጽምልን ዘንድ በቀጣይነት በየእለቱ እራሳችንን ለክርስቶስ አሳልፈን እንድንሰጥ እባክህ እርዳን፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-** በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች፣ እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

**2ኛ ቀን**

**ስለ የእግዚአብሔር ስጦታ ግንዛቤ ማግኘት**

‹‹… ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን… የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ…›› (ኤፊሶን 3፡18-19)

**ተቀበሉ፤ እራሳችሁን አሳልፋችሁ ስጡ፤ እደጉ**

የእግዚአብሔርን ፍቅር በሙላት መለማመድ የምንችለው እንዴት ነው? ጳውሎስ በኤፌሶን 3፡14- 21 የሚለውን አንብቡ፡፡

1. በመጀመሪያ ደረጃ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ መቀበል ያስፈልገናል፡፡ ‹‹በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ…. እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ …›› (ቁጥር 16)
2. ቀጥሎ ‹‹ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር›› (ቁጥር 17) እንደተባለው ሕይወታችንን ለክርስቶስ አሳልፈን በመስጠት ቀጣይነት ባለው የጠበቀ ቅርርቦሽ ከእስ ጋር እንመላለሳለን፡፡
3. ከዚያም በክርስቶስ እና በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር ምክንያት እምነታችን እያደገ እና እየበሰለ ይሄዳል፡፡ የእኛም ‹‹ሥርና መሠረት በፍቅር [የጸና]›› ይሆናል (ቁጥር 17)

*ታዲያ ውጤቱ ምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ፍቅር በሙላት የምንለማመድ መሆናችን ነው፡፡* ‹‹ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን … የክርስቶስ ፍቅር ለማወቅ›› የሚያስችለንን ኃይል እሱ ይሰጠናል (ቁጥር 18)፡፡

**የእግዚአብሔር ፍቅር በእያንዳንዱ ነገር ተፈትኖ የሚያልፍ ነው**

በሉቃስ 15፡11-32 ያለውን የአባካኙን ልጅ ምሳሌያዊ ታሪክ አስቡ፡፡ አንድ ቀን ታናሽየው ልጅ  በእግዚአብሔር ምሳሌነት ወደተቀመጠው አባቱ ሄዶ ከቤት መውጣት እና የእራሱን ኑሮ መኖር እንደሚፈልግ ገለጸለት፡፡ ይህም የቤተሰቡ መመሪያዎች (በተመሳሳይ የእግዚአብሔር ትእዛዛት) እንዳልተስማሙት በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ልጁ የጠየቀው በዚያ ወቅት መውረስ የማይገባውን ውርስ ነበር፤ አባቱ ግን ድርሻውን ሰጠው፡፡ አባቱ ሙሉ ነፃነት የሰጠው ይወደው የነበረ በመሆኑ እና ምርጫውን በማክበሩ ነው (እግዚአብሔር ለእኛ እንደሆነው እና እንደሚያደርገው ሁሉ ማለት ነው)፡፡

ከዚያ በኋላ ልጁ ወደ ሩቅ ስፍራ ተጉዞ ገንዘቡን በፈንጠዝያ እና በልቅ ሴቶች ላይ ማዋል ያዘ፡፡  ገንዘቡ እየቀነሰ ሲሄድ የወዳጆቹ ቁጥር እያነሰ ሄዶ፣ በመጨረሻ ምንም የሌለው ሆነ፡፡  ይባሱኑም፣ ይኖርበት የነበረው አካባቢ በረሀብ ተጠቃ፡፡  ሕይወቱን ለማቆየት ጭንቅ ውስጥ ገብቶ ሥራ መፈለግ ያዘ፤ ያገኘው ሥራ ግን የአሣማዎች እረኝነት ብቻ ነበር፡፡ በረሀብ ሲሰቃይ የአሣማዎቹን ምግብ ለመብላት እንኳ አይፈቀድለትም ነበር፡፡  ከባድ ሁኔታዎች በሚገጥሙ ጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ፣ ሕይወቱን ማጤን ጀመረ፡፡  እሱ እንዲያ የተራበው የአባቱ አገልጋዮች በሙሉ የሚያስፈልጋቸውን ያህል እየበሉ ሳለ እንደነበረ ተገነዘበ፤ እናም ወደ አባቱ ሄዶ እንዲህ ሊለው ለእራሱ ቃል ገባ፡- ‹‹አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፤ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ››  (ቁጥር 18፣19)

ልጅየው ወደ ቤቱ ያቀናው በድብልቅ ስሜት ነበር፤ አባቱ ግን ቀድሞውኑ እየጠበቀው ነበር፡፡  አባትየው ርኅራኄ ተሞልቶ ወደ ልጁ በመሮጥ አንገቱን አቅፎ ሳመው፤ ይኸውም ምንም እንኳ ልጁ  የቆሸሸ  እና መጥፎ ጠረን የነበረው ሳይሆን ባይቀርም ነው፡፡ ልጁ ኑዛዜውን ገና ሳይጨርስ፣ አባትየው አገልጋዮቹን ምርጥ ልብሶች እንዲያመጡለት እና ድግስ እንዲያዘጋጁ ነገራቸው፡፡  ልጁን ቀድሞ ለእሱ በነበረው ፍቅር እንደወደደው ግልጽ ነው፡፡  በዚህ ታሪክ የምናገኘው መላውን የድነት ታሪክ ነው፤ ይኸውም የሐጢአተኛን ንስሐ እና ኑዛዜ፣ እንዲሁም በናፍቆት ሲጠባበቀው የቆየውንና ሲመለስ በታላቅ ደስታ አቀባበል ያደረገለትን አባት ታሪክ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚወደን ሁኔታዎችን ሳያስታክክ ነው! ሆኖም ልክ ልጅየው ተመልሶ ወደ አባቱ እንደሄደ፣ እኛም ወደ እግዚአብሔር መሄድ ያስፈልገናል፡፡

አባትየው ፍቅሩን ለልጁ ማፍሰስ የተቻለው ልጁ በተመለሰ ጊዜ ብቻ ነው፡፡  ልጁ አባቱ ሊሰጠው የፈለገውን ለመቀበል ክፍት የሆነው ያኔ ነበር፡፡  በመጨረሻም፣ በመካከላቸው በነበረው ጥብቅ ቅርርቦሽ ጣልቃ የሚገባ ነገር ሳይኖር፣ ልጅየው ሳይቦዝን ሲጠብቀው የነበረው አባቱን መልካምነት መለማመድ ቻለ፡፡

ወደ ጥያቄያችን እንመለስ፡፡ ‹‹የእግዚአብሔርን ፍቅር በሙላት የምንለማመደው እንዴት ነው?›› በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እለት በእለት እራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ አሳልፈን በመስጠት በመመላለስ ነው፡፡ ሕይወታችን በእግዚአብሔር ፍቅር ሲሞላ ደግሞ ፍቅሩን ለሰዎች የምናስተላልፍ እንሆናለን፡፡ ኤለን ኋይት እንዲህ ትላለች፡- ‹‹ሐዋርያትን በአንድነት ባስተሳሰረው በእነሱ ዘንድ የነበረ ፍቅር በየእለቱ መጠመቅ ያስፈልጋችኋል፡፡›› (Testimonies for the Church, vol. 8, p. 191)

ይህንን መለኮታዊ ፍቅር መረዳት እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ‹‹ሰዎች ክርስቶስን መውደድ ወይም መስቀሉን በእምነት ዐይን መመልከት እንዲችሉ፣ የእሱን ባሕርይ ማየት ወይም ማስተዋል እንዳለባቸው ጳውሎስ ተረድቶ ነበር፡፡ መቤዠትን ያገኙ ሰዎች በዘላለም ዘመናት አዳዲስ ግኝቶች የሚያገኙበት እና ዝማሬ የሚሆንላቸው ጥናት መጀመር ያለበት ከዚህ ነው፡፡››  (The Acts of the Apostles, p. 273) ብዙ ገጽታዎች ያሉትን ወደር የሌለው የአዳኛችን ፍቅር ማጥናት እንዴት ያለ ሐሴት ነው! ታዲያ ዛሬ ዐይናችሁን ወደ የሱስ ማዞርን ምርጫችሁ አታደርጉም?

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

***ታላቂቱ ትእዛዝ የትኛይቱ ናት?***

‹‹ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብኅ፣ በፍጹም ነፍስህም፣ በፍጹም አሳብህም ወደድ፡፡…
ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፤ እርስዋም፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስ ውደድ የምትለው ናት፡፡›› (ማቴዎስ 22፡37፣39)

*አባት ሆይ፤ ስለምትወደኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ እባክህ በፍጹም ልቤ፣ በፍጹም እኔነቴ፣ በፍጹም ስሜቴ፣ እና በፍጹም ኃይሌ እንድወድህ እርዳኝ፡፡ ይህ ልመናዬን እንደ ፈቃድህ ስለመለስህልኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ በአንተ እርዳት ባልንጀራዬን ለመውደድ ፈቃዴ ነው፡፡ የአንተን ፍቅር ለሰዎች የማስተላልፍ አድርገኝ፡፡*

**ስለ የእግዚአብሔር ፍቅር ጥልቀት ግንዛቤ ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?**

‹‹በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ፣ ክርስቶም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፣ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፣ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ፡፡›› (ኤፌሶን 3፡16-18)

*አባት ሆይ፣ በመንፈስ ቅዱስህ ከውስጣዊ ሕይወቴ እስከ ውጫዊ ሕይወቴ ባለኝ ማንነት ታበረታኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፡፡ ክርስቶስ በእምነት በሕይወቴ ኖሮ እየመራኝ፣ በእሱ ፍቅር ፍጹም መተከል ልቻል፡፡ ይህ ልመናዬ ከፈቃድህ ጋር የተሰማማ እንደመሆኑ፣ ስለሰማኸኝ እና ስለመለስህልኝ አመሰግንሃለሁ፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደገሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና እሱ ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጊዜ ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-** በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውስኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**የአካባቢያችሁ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

**3ኛ ቀን**

**ቁልፉ እራስን አሳልፎ መስጠት ነው**

‹‹… ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ [አቅርቡ]… እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው፡፡›› (ሮሜ 12፡1)

**የሕይወት ጉዞዬ**

በንግድ ሥራ የተሰማራሁ የ36 ዓመት ጎልማሳ እያለሁ ነበር በድንገት ፓስተር የነበረው ጓደኛዬ በ41 ዓመቱ በሞት የተለየኝ፡፡ ይህ ክስተት ወደ አዕምሮዬ እንዲህ የሚል ጥያቄ አመጣብኝ፡- ‹‹እግዚአብሔር ለፓስተርነት ቢጠራኝ የሚሆነው ምንድን ነው?››፡፡ ይህ የምፈልገው ነገር በፍጹም አልነበረም፡፡ ሳምንቱን ሙሉ፣ በጠዋት፣ በቀትር፣ እና በሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር አምርሬ ስታገል እና ስደራደር ቆየሁ፡፡ እንዴት በሌሎች መንገዶች ላገለግለው እንደምችል አስረዳሁት፡፡ እግዚአብሔር

ተቃውሞዎቼን ያልተቀበለልኝ መሆኑ ግልጽ ነበር፤ እናም ሙግቴን አቁሜ በአልጋዬ አጠገብ ተንበርክኬ እያለ፣ አንድ ነገር በጸጥታ ወደ አዕምሮዬ እንዲህ ሰተት አለ፦ ‹‹እግዚአብሔር ይወድሃል!››፡፡ እኔም ‹‹ይህንን አምናለሁ!›› አልኩ በውስጤ፡፡

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በእግዚአብሔር ፍቅር መታመን አድሮብኝ፣ ሙሉ በሙሉ እራሴን ለእሱ አሳልፌ ለመስጠት በቃሁ፡፡ ከዚያም ሰላም አገኘሁ፡፡ በእርግጥም፣ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ጌታ ፓስተር እንድሆን ጠራኝ፡፡ ይህ ከሆነ ብዙ ዓመታት ባለፉበት በአሁኑም ወቅት፣ ስለዚህ ጉዳይ ለእግዚአብሔር ከፍ ያለ አመስጋኝነት ይሰማኛል፡፡ እሱ ማለቂያ በሌላቸው ፍቅሩ እና ጥበቡ ነበር እኔ ካሰብሁት ሙሉ በሙሉ ወደተለየ አቅጣጫ ያመላከተኝ፡፡ እንዲህ እራሴን አሳልፌ መስጠቴ በሕይወቴ ታላላቅ በረከቶች ያስገኘልኝ መሆኑን እያየሁ ነው፡፡ እግዚአብሔር የመራኝ ምርጥ ወደነበረው መንገድ ነው፡፡

**እራስን አሳልፎ መስጠት ለምን ያስፈልጋል?**

ጋሪ ኤፍ ዊልያምስ እንደጻፈው፣ ‹‹ሙሉ በሙሉ እራስን አሳልፎ መስጠት ለድነት፣ ዳግም ለመወለድ፣ በሐጢአት እና በፈተና ላይ ድል ለማግኘት፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን በሙላት ለማግኘት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡›› (How to be Filled with the Holy Spirit and Know It) ይህ ፍጹም አፅንዖት ያለበት መልእክት ነው፡፡

እግዚአብሔር እኔን ሙሉ ለሙሉ ሊጠቀምብኝ እንዲችል እራሴን ለእሱ አሳልፌ መስጠት የነበረብኝ እንደመሆኑ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ እያለ እግዚአብሔር ጥሪ ባቀረበለት ወቅት የቀድሞ ሕይወቱን እና እቅዶቹን መተው ነበረበት፡፡ ኋላ ላይ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ‹‹ሰውነታችሁን ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ››፣ እንዲሁም ‹‹ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤›› በማለት አማኞችን ወትውቷል፡፡ (ሮሜ. 12፡1፤ 6፡13)

አብዛኛውን ጊዜ ካለማወቅ የተነሳ፣ ብዙ ሰዎች እራሳቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው የሰጡ አይደሉም፤ ይልቁኑ ሕይወታቸውን የሚመሩት እራሳቸው ናቸው፡፡ ሌሎቹን የእግዚአብሔር ስጦታዎች ሁሉ የሚያስገኘው የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይጎድላቸዋል፡፡ ‹‹ሆኖም ልክ እንደማንኛውም ሌላ የተስፋ ቃል፣ ይህን ስጦታ ለማግኘት መሟላት የሚገባው መስፈርት አለ፡፡ የጌታን የተስፋ ቃል የሚያምኑ እና በእምነት የእራሳቸው ማድረጋቸውን የሚስታውቁ ብዙ ሰዎች አሉ፤ ስለ ክርስቶስ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ያወራሉ፤ ሆኖም ምንም ጥቅም አያገኙበትም፡፡ በመለኮታዊ ተፅእኖዎች ምሪት እና ቁጥጥር ውስጥ ለመዋል እራሳቸውን አሳልፈው አይሰጡም፡፡›› (The Desire of Ages, p. 672)

እንደ ሰብአዊ ፍጡራንነታችን ነፃነታችንን ላለመልቀቅ እንታገላለን፤ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ምኞት ግን ከዚህ ተቃራኒ ነው፦ ‹‹እግዚአብሔር ሊፈውሰን እና ነፃ ሊያወጣን ይመኛል፡፡ ሆኖም ይህ ሙሉ በሙሉ መለወጥን፣ በመላ ተፈጥሯችን መታደስን የሚጠይቅ እንደመሆኑ፣ ሙሉ በሙሉ እራሳችንን ለእሱ አሳልፈን መስጠት አለብን፡፡›› (Steps to Christ, p. 43)

የሐጢአት ሕይወት እኛ ልንስለው እንደምንፈልገው የነፃነት ሕይወት አይደለም፡፡ ‹‹እራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ለመስጠት የማይፈቅድ እያንዳንዱ ሰው በሌላ ኃይል ቁጥጥር ስር የሚውል ነው፡፡ የእራሱ አይደለም፡፡ ስለ ነፃነት ሊያወራ ይችላል፤ ግን እጅግ አስከፊ በሆነ ባርነት የሚመላለስ ነው፡፡ ሀሳቡ በሰይጣን ቁጥጥር ውስጥ ያለ በመሆኑ፣ የእውነትን ውበት ማየት አይቻለውም፡፡ ‹የእራሴን ማመዛዘን እየተጠቀምሁ ነው› በሚል እሳቤ እራሱን ቢሸነግልም፣ እየታዘዘ ያለው ለጨለማው ልዑል ፈቃድ ነው፡፡ ክርስቶስ የመጣው የሐጢአት ባርነት ማነቆዎችን ከሰዎች ለማላቀቅ ነው፡፡›› (The Desire of Ages, p. 466)

እራሳችንን ለክርስቶስ አሳልፈን በመስጠት የምናጣው ምንድን ነው? እሱ ከእራስ ግዞተኝነት ነፃ ሊያወጣን ይቻለዋል፤ ይኸውም ከቅናት፣ ከቁጭት፣ ከጠበኝነት፣ ከስስት፣ ከሱስ፣ ከቁጣ፣ ከትዕቢት፣ ከከንቱ ትምክህት፣ ከተስፋ መቁረጥ፣ ከበታችነት ስሜት፣ ወዘተ ነው፡፡ እያንዳንዳቸው ሰብአዊ ፍጡራን የእየራሳቸው ዋና ችግር መሆናቸውን አስታውሱ፡፡ የእርስዎ

*ትልቁ ችግር እራስዎ ነዎት፡፡ ‹‹ሰው እራሱን ለክርስቶስ አሳልፎ በመስጠቱ በሚያገኘው የሕይወት ለውጥ ትልቅ የነፃነት እፎይታ ይኖረዋል፡፡›› (The Desire of Ages, p. 466)*

*ነገር ግን ሸክላ ሠሪ መሥራት የሚችለው በእጁ ውስጥ ባለው የሸክላ አፈር ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው እራሳችንን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው፡፡ ‹‹ኃይሎቻችንን በመላ ለእግዚአብሔር አሳልፈን መስጠታችን የሕይወትን ችግር በእጅጉ የሚያቃልልን ነው፡፡ ከተፈጥሯዊው ልብ ምኞቶች ጋር የምናደርጋቸውን በሺህ የሚቆጠሩ ግብግቦች የሚያረግብ እና የሚያቅብ ነው፡፡›› (My Life Today, p. 6)*

*ወደ ዘላቂ ሐሴት የሚያደርሰው አካሄድ እራስን አሳልፎ መስጠት ብቻ ነው፡፡ ‹‹ክርስቶስ በቃሉ ታማኝ እንደሆነ የሚያምኑ እና ነፍሳቸውን ለእሱ ጥበቃ፣ ሕይወታቸውንም በመላ ለእሱ አሳልፈው የሚሰጡ ሰዎች ሰላም እና መረጋጋት ይኖራቸዋል፡፡ የሱስ በመገኘቱ ደስታ እያስገኘላቸው ሳለ፣ በዓለም ያለ ምንም ነገር ሀዘንተኛ ሊያደርጋቸው አይችልም፡፡ ፈቃድን ሙሉ በሙሉ በመስጠት ፍጹም እረፍት ይገኛል፡፡››  (The Desire of Ages, p. 331) ዛሬ ክርስቶስ ይህንን ፍጹም እረፍት እንድትለማመዱ ይጋብዛችኋል!)*

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

**የፍቅርህ መሣሪያዎች አድርገን**

*‹‹ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፤ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ፡፡›› (ሮሜ. 6፡13)*

*ጌታ ሆይ፤ እያንዳንዱን የሕይወታችን ክፍል ልንሰጥህ እንወዳለን፡፡  ለክብርህ የምንውል መሣሪያዎች አድርገህ ተጠቀመብን፡፡*

**በምንኖረው ሕይወት እንድናመልክህ እርዳን**

*‹‹እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው፡፡›› (ሮሜ 12፡1)*

*አባት ሆይ፤ አዲስ ፍጥረት ሆነን እንድንመላለስ ስለጋበዝኸን እጅግ እናመሰግንሃለን፡፡  በየእለቱ ያለ ምንም መቆጠብ እራሳችንን ለአንተ አሳልፈን እንዴት መስጠት እንደምንችል አሳየን፡፡  ባንተ ብርታት በሁሉም ነገር የምንከተልህ እንድንሆን እርዳን፡፡*

**ከክፉው ተከላከልልን**

*‹‹ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ሐጢአት እንደማያደርግ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚጠብቀው፣ ክፉውም እንደማይነካው እናውቃለን፡፡›› (1ዮሐንስ 5፡18 አ.መ.ት)*

*ጌታ ሆይ ለአንተ እራሳችንን አሳልፈን ስንሰጥ ከክፉው እንደምትከላከልልን ቃል ስለገባህ እና መስግንሃለን፡፡  ወደ ፍጹም ሐሴት በሚያደርሰው መንገድህ ምራን፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና እግዚአብሔር ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-** በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት  የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

**4ኛ ቀን**

**ተሃድሶን በተግባር መለማመድ**

‹‹አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ ትለምናላችሁ፤ በምቾቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም፡፡›› (ያዕቆብ 4፡2፣3)

**ምን ዓይነት ነገሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ አስቡ**

በቤተ ክርስቲያናችሁ የተሃድሶ ስብከት በማቅረብ ላይ ያለ ሰውን በምናባችሁ ሳሉ፡፡  ሰባኪው በመጨረሻ ጥሪው አዳማጮቹን የሱስን ተቀብለው ሁልጊዜ እንዲከተሉት ይጋብዛቸዋል፡፡  ምናልባት ምላሽ  የሚሰጥ ሰው ላይኖር ይችላል፡፡ ምናልባትም ጥቂት ሰዎች ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ ብዙ ሰዎች፡፡  እግዚአብሔር ሰብአዊ ፍጡራንን የፈጠረው ከነፃ ምርጫ ጋር እንደመሆኑ፣ ሰዎች ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚሰጡ እርግጠኛ መሆን አንችልም፡፡  ሆኖም በገሃድ በምናስተላልፈው ስብከት፣ በግላችን ለሰዎች በምንሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ በወዳጃዊ ምስክርነታችን፣ ወይም ባልተጠበቁ መለኮታዊ ክስተቶች አማካይነት ሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ተቀብለው ከተገበሩት፣ ምስክርነታችን ስኬታማ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡  እንዲህ ያለው ውጤታማነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው፡፡  እኛ ግን ከኋላ ሆነን እግዚአብሔር የሚያከናውናቸውን ተዓምራት በአድናቆት የምናይ ነው የምንሆነው፡፡

እጅግ ብዙ ጊዜያት የምንኖረው የክርስትና ሕይወት ከውጤታማነት እጅግ የወረደ ነው፡፡  ይህ ግን የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞቻችን እና ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ የምናወጣቸው እቅዶች ከንቱ ናቸው ማለት አይደለም፡፡፡ በልባዊነት የምንተገብራቸውን ሰብአዊ ጥረቶች ጌታ ወደ እሱ የተዘረጋነውን ያህል የባረካቸው መሆኑ እርግጥ ነው፡፡  ሆኖም የመንፈስ ቅዱስን መውረድ በሙላት ብንለማመድ ምንኛ የላቀ ልምምድ ይኖረን ነበር! ይህ ቢሆን ኖሮ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ነገሮችን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው! ሰባኪው ሄንሪ ቲ ብላካባይ እንዲህ ጽፏል፡-  ‹‹በእራሳችን ብርታት እና ጥበብ በስልሳ ዓመታት ከምናከናውነው በበለጠ፣ ጌታ  እራሳቸውን ለእሱ አሳልፈው በሰጡ ሰዎች በስድስት ወራት›› ቆይታ የሚያከናውነው ይበልጣል፡፡ (Blackaby, Experiencing God, p. 108, revised edition)

ለተሃድሶ መጸለይ አስፈላጊ ነው፤ ሆኖም በዚህ ብቻ ማቆም አይቻለንም፡፡  በየግላችሁ ተሃድሶን በትክክል ለመለማመድ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች እንድትወስዱ እጋብዛችኋለሁ፡፡  በእግዚአብሔር በረከት ሕይወታችሁ ከዚህ ቀደሙ የበለጠ ኃይል የተሞላ እና ትርጉም ያለው ሊሆን ይችላል፡፡  በቤታችሁ እና በቤተ ክርስቲያናችሁም የአዲስ ሕይወት ልምምድን ማግኘት ይሆንላችኋል፡፡

**የጎደለው ምንድን ነው?**

በመጀመሪያ፣ ጥቂት ጥያቄዎችን እንጠይቅ፡- የችግሮቻችን ማዕከል ምንድን ነው? መንፈሳዊ ነው?

ለብ ያለው የክርስትና ልምምዳችን ስረ-መሠረት የመንፈስ ቅዱስ እጦታችን ሊሆን ይችላል? መልሱ ‹‹አዎ›› ከሆነ፣ ታዲያ የመንፈስ ቅዱስ እጦት የደረሰብን እንዴት ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ፡- ‹‹አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ ትለምናላችሁ፤ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም፡፡›› (ያዕቆብ 4፡2፣3) በሕይወታችን መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት በቀጣይነት እንድንጸልይ እግዚአብሔር እንደሚጋብዘን ከ1ኛው ቀን ንባብ ተምረናል፡፡ ‹‹ታዲያ ኃይልን የምንቀበለው በዚህ መንገድ እንደመሆኑ፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የማንራበው እና የማንጠማው ለምንድን ነው? ደግሞስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የማንነጋገረው፣ የማንጸልየው፣ እና የማንሰብከው ለምንድን ነው?›› (Testimonies for the Church, vol. 8, p. 22)

ያዕቆብ በተጨማሪ የሚያሳስበን የምንለምነው በእራስ ወዳድነት ለእራሳችን ምኞት ለማግኘት ብለን ሲሆን፣ የምንለምነውን እንደማናገኝ ነው፡፡ እዚህ ላይ እያለ ያለው፣ እግዚአብሔር ልባችንን ያሳረፍነው ‹‹በሥጋ ነገሮች›› ላይ ሲሆን፣ ሊባርከን እንደማይችል ነው፡፡ ‹‹ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፤ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው፡፡›› በማለት ጳውሎስ ነገሩን አብራርቷል፡፡ (ሮሜ 8፡5፣ 6)

ጳውሎስ ‹‹ስለ ሥጋ ማሰብ›› ያለው ምንድን ነው? በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሦስት ዓይነት የሰዎች ቡድኖች እና በየቡድኑ ያሉት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው ግንኙነት ይናገራል፡፡ ከወላጅ ከሚገኝ የሕይወት ስልጠና፣ በዘረመል ውርስ ከሚገኝ ባሕርይ፣ እራስን ከመቆጣጠር አቅም፣ ከእድሜ፣ ከባሕል፣ ከትምህርት ደረጃ፣ ወዘተ አኳያ በየቡድኑ ባሉ ሰዎች መካከልም እንኳ ብዙ ልዩነቶች አሉ፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ቢኖሩም፣ በመሠረታዊነት የምናገኘው ሦስት ቡድኖችን ነው፡- ‹‹ተፈጥራዊ›› ወይም ‹‹ዓለማዊ›› ሰው፣ ‹‹መንፈሳዊ›› ወይም ‹‹በመንፈስ የተሞላ›› ሰው፣ እንዲሁም ‹‹ሥጋዊ›› ሰው፡፡

በ1 ቆሮንቶስ 2፡14- 16 እና 3፡1- 4 እነዚህ ሦስት ቡድኖች ተገልጸዋል፡፡ አሁን በእግረ መንገድ የምናነሳው ተፈጥሯዊውን ሰው ነው፤ ይህ ሰው በዓለም እየኖረ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግንኙነትን ገና ያላገኘ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባላት ደግሞ በተቀሩት ሁለት ቡድኖች የሚገኙ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸውን ቡድኖች ለመግለጽ የዋሉትን ስሞች ማየት ብቻ በዋንኛነት የእያንዳንዳቸው ችግር የተሰወረው በምን ውስጥ እንደሆነ ለመረዳት ይረዳል፡፡ ታዲያ ጥያቄው መሆን ያለበት ‹‹በየትኛው ቡድን ነው የምገኘው?›› ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ባጭሩ ሕይወትን መፈተሽ እራስን ለመመርመር ይረዳል፤ ይህ ሲደረግ ግን፣ ጥረታችን የየግዛ እራሳችንን እንጂ የሌሎች ሰዎችን ሕይወት ለማየት እንዳይደለ ማስታወስ ይገባል! በየግላችሁ ምን ዓይነት ሰው እንደሆናችሁ አስቡ፡፡

**ተፈጥሯዊ፡**- ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት [ስለሚሆንበት] አይቀበለውም፤›› (1ቆሮንቶስ 2፡16)

***መንፈሳዊ፡***- ከእግዚአብሔር ጋር የተሟላ እና እውነተኛ ግንኙነት ያለው ነው፡፡ መንፈሳውያን ስንሆን፣ ‹‹የክርስቶስ ልብ [ያለን]›› እንሆናለን፡፡ (1 ቆሮንቶስ 2፡16)

***ሥጋዊ፡***- ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በማስመሰል ወይም በተከፋፈለ ልብ የሚይዝ ነው፡፡ ‹‹እኔም ወንድሞች ሆይ፤ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፣ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም፡፡›› (1 ቆሮንቶስ 3፡1)

በ5ኛው ቀን የምናየው ሀሳብ፡- በመንፈሳዊ ክርስቲያን እና በሥጋዊ ክርስቲያን መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

***በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ***

***መንፈስ ቅዱስ ሀሳባችንን ይመራል***

‹‹እንደ *ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፤* እንደ *መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ፡፡›› (ሮሜ 8፡5)

*አባት ሆይ፤ ወይ በሥጋችን ወይም በመንፈስ ቅዱስ ተፅእኖ ውስጥ የምናድር መሆናችንን እናውቃለን፡፡ እባክህ መንፈሳዊ ክርስቲያኖች በመሆን የመንፈስን ነገር እንድናስብ እርዳን፡፡*

**ከእንግዲህ ወዲህ በ*ሥጋዊ* ምኞቶቻችን የምንነዳ አይደለንም**

‹‹እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ *የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም*።›› (ገላትያ 5፡16 አ.መ.ት)

*ጌታ ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ያለውን የሐጢአት ኃይል ስለሚሰብርልን እናመሰግንሃለን፡፡ እባክህ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ በልባችን አፍራ፡፡ ስለዚህ ግሩም የተስፋ ቃል እናመሰግንሃለን፡፡*

***መንፈስ ቅዱስ* ከኩነኔ ይታደገናል፡-** ‹‹እንግዲህ፣ እንደ *ሥጋ ፈቃድ* ሳይሆን፣ እንደ *መንፈስ ፈቃድ* የሚመላለሱ በክርስቶስ የሱስ ያሉ ሰዎች ኩነኔ የለባቸውም፡፡ በክርስቶስ የሱስ ያለው የሕይወት *መንፈስ* ሕግ ከኃጢአት እና ከሞት ሕግ ነፃ አውጥቶኛልና›› (ሮሜ 8፡1፣2 ለኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ ቀረብ ያለ ትርጉም)

*አባት ሆይ፤ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ስንመላለስ የሐጢአት እስራት የሚበጠስልን መሆኑን መረዳት ምንኛ በረከት ነው፡፡ ክርስቶስ በደላችንን በእራሱ ላይ አድርጎ ከሐጢአት እና ከሞት ነፃ ሰላወጣን እናመሰግንሃለን፡፡*

***ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች***

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት**፡- በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እንዲሁም ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

**5ኛ *ቀን***

***መንፈሳዊ ወይስ ሥጋዊ፡- ልዩነቱ ምንድን ነው?***

‹‹...እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን፡፡›› 1 ቆሮንቶስ 2፡16

***ከሰማይ ጋር ያለን ተያያዥነት***

‹‹መንፈሳዊ ክርስቲያን›› እና ‹‹ሥጋዊ ክርስቲያን›› ለሚሉት ሐረጎች ትርጉሞች ከመስጠታችን በፊት፣ እየተነጋገርን ያለነው ‹‹ሐጢአተኛ የሆኑ ሰዎች›› እና ‹‹ሐጢአተኛ ያልሆኑ ሰዎች›› በሚል ፍረጃ እንዳልሆነ ማስታወስ ያስፈልገናል፡፡ መንፈሳዊም ሆኑ ሥጋዊ፣ ሁሉም ሰዎች አዳኝ የሚያስፈልጋቸው ሐጢአተኞች ናቸው፡፡ ጽድቃችን የሚመጣው ከእሱ ብቻ ነው፡፡ ይልቁኑ፣ በአንዱ ወይ በሌላው ቡድን የሚከተን በግላችን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት ይዞታ ነው፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት ስንቆርጥ፣ ከሰማይ ጋር ያለንን መያያዝ ላይ እክል ማምጣታችን እንደማይቀር እግዚአብሔር አፅንኦት ሰጥቷል (ማቴዎስ 12፡32)፡፡ ኤለን ኋይት ነገሩን እንዲህ አብራርታለች፡- ‹‹የመንፈስ ቅዱስን አሠራር የሚገፋ ሰው ወደ ንስሐ እና ወደ እምነት የማይመራው ሁኔታ ውስጥ እራሱን እየከተተ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሰው ልብ የሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው፡፡›› (The Desire of Ages, p. 322)

ይህንን መድገም ተገቢ ነው፡- መንፈሳዊ ወይም ሥጋዊ ብዬ መለየት የምችለው እራሴን ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር አንደ እኔው በሌሎች ሰዎች ልብ መሥራት የሚቻለው እንደመሆኑ፣ እኔ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ላይ ስም መለጠፍ አያስፈልገኝም፡፡ እግዚአብሔር ያልተገነዘብሁትን አሳዛኝ ይዞታዬን በልቤ ሲያስታውቀኝ፣ መልካም ዜና አለ፤ ይኸውም ከዛሬውኑ ጀምሮ ሊለውጠኝ የሚቻለው መሆኑ ነው!

**መንፈሳዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አባል**

መንፈሳዊ ሰው በእውነት የተለወጠ ክርስቲያን ነው፡፡ ምንም እንኳ ሐጢአተኛ ተፈጥሮ ይዞ የተወለደ ቢሆን፣ ‹‹መንፈሳዊ›› መባል የቻለው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕያው የሆነ የሚያድግ ግንኙነት ያዳበረ ስለሆነ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ጽፏል፡- ‹‹መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል፤ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም፡፡ እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን፡፡›› (1 ቆሮንቶስ 2፡15፣16)

በመጀመሪያ ጥቂት ጥያቄዎች እንጠይቅ፡- የችግሮቻችን ሁሉ ማዕከል ምንድን ነው? መንፈሳዊ ነው? የመንፈስ ቅዱስ እጦታችን ያለው ሉብ ባለው የክርስትና ልምምዳችን ነው? መልሱ አዎ ከሆነ፣ ታዲያ በሕይወታችን የመንፈስ ቅዱስ እጦት እንዲኖር ለምን እንፈቅዳለን?

የመንፈሳዊው ሰው ሕይወት ማዕከል የሱስ ሲሆን፣ በሰውየው ልብ ከፍተኛውን ስፍራ ይዞ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡትን ነገሮች በቁርጥ ያስቀምጥለታል፡፡ ሙሉ በሙሉ እራሱን ለየሱስ የሰጠ ሲሆን፣ በመንፈስ ሙላት ለመመላለስ በቀጣይነት ይጸልያል (ሉቃስ 11፡13)፡፡ መንፈሳዊው ሰው በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዐውድ ሲታይ፣ ‹‹ትኩስ›› ተብሎ ሊጠራ ይችላል (ራእይ 3፡15)፡፡ ከአስሩ ቆነጃጅት ምሳሌያዊ ታሪክ አንፃር ደግሞ ‹‹ልባም/ጠቢብ›› ተብሎ ሊጠራ ይችላል (ማቴዎስ 25፡2-4)፡፡ መንፈሳዊው ሰው ‹‹የተትረፈረፈ ሕይወትን›› (ዮሐንስ 10፡10) የሚለማመድ ሲሆን፣ ‹‹በእግዚአብሔር ፍጹም ሙላት›› የተሞላ ነው (ኤፌሶን 3፡19)፡፡ ‹‹በእምነት የዳነ›› በመሆኑ ሐሴት ያደርጋል (ኤፌሶን 2፡8)፡፡ ምንም እንኳ መንፈሳዊው ሰው እንቅፋቶች እና ፈተናዎች ያሉበት ቢሆን፣ ዐይኖቹን የሚተክለው በየሱስ ላይ ነው፡፡

**ሥጋዊ የቤተ ክርስቲያን አባል**

ሥጋዊ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በማስመሰል ወይም በተከፋፈለ ልብ የሚይዝ ነው፡፡ በግልጽ ባይሆንም፤ ለመንፈስ ቅዱስ ግድ የለሽነት ያለው ወይም ደግሞ ግለጽ ዐመፀኝነት የሚታይበት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡- ‹‹እኔም ወንድሞች ሆይ፤ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፣ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም፡፡ ገና ጽኑ ሙብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና፤ እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም፡፡ ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን? አንዱ፡- እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ ሁለተኛውም፡- እኔ የአጵሎስ ነኝ፤ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?›› (1 ቆሮንቶስ 3፡1-4)

ይህ ገለጻ የሚያስገኝልን ድምዳሜ ወሳኙ ነገር ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት መሆኑን ነው፡፡ *ሥጋዊ* የሚለው ቃል የሚገልጸው በስጋዊ ሀሳብ የሚመራ ሰውን ነው፤ ይህም፣ ይህ ሰው የሚደገፈው በመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን፣ በተለመደው ሰብአዊ ኃይል ነው ማለት ነው፡፡ ትልቁ አሳዛኝ ነገር ደግሞ ዘላለማዊ ሕይወትን ለማግኘት አለመምረጡ ነው (ሮሜ 8፡9)፡፡

ጳውሎስ *ሥጋዊ* ሰዎችን ‹‹ወንድሞች›› ብሎ መጥራቱ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንደነበሩ የሚያሳይ ነው፡፡ በበቂ መጠን በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ የነበሩ በመሆናቸው ‹‹መንፈሳውያን›› ብሎ ሊጠራቸው አልቻለም፡፡ እንደሚገባቸው በእምነት ያደጉ አልነበሩም፡፡ ለብዙ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን እየቆዩ *ሥጋዊ* ክርስቲያን በመሆን መቀጠል ይቻላል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ኖሮ መንፈሳዊ ብስለት ሳያገኙ መቀጠል ይቻላል፡፡ ብዙ *ሥጋዊ* ክርስቲያኖች ያለ እርካታ፣ በተስፋ መቁረጥ፣ ወይም የመንፈሳዊ ሕይወት ዓላማ ሳይዙ የሚመላለሱ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደስታ ርቋቸው፣ ፍላጎትም አጥተው ‹‹እንግዲህ ሐጢአተኞች ነን፤ ምንም ማድረግ አንችልም›› ብለው የተቀመጡ ናቸው፡፡

ሌሎች *ሥጋዊ* ክርስቲያኖች ደግሞ በፍላጎት እና በንቁ እንቅስቃሴ እየተመላለሱም፣ ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን ባሏቸው ትላልቅ ቦታዎች የሚኩራሩ ናቸው፡፡ የሚያሳዝነው ግን፣ እውነታው የሱስ እንዲህ እንዳለው መሆኑ ነው፡- ‹‹በዚያ ቀን ብዙዎች፡- ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፣ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል፡፡ የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፤ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ፡፡›› (*ማቴዎስ* 7፡22፣23) ችግሩ ምን ነበር? ከየሱስ ጋር የግል ግንኙነት ያልነበራቸው እና ሕያው በሆነ መያያዝ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕብረት ያልነበራቸው መሆናቸው ነበር፡፡

*ሥጋዊ* ክርስቲያን ሆናችሁ እራሳችሁን ያገኛችሁ ከሆነ፣ አይዟችሁ! አሁኑኑ አዲስ ሕይወት የመጀመር ዕድል አላችሁ፡፡ ብዙ *ሥጋዊ* ክርስቲያኖች ሳያውቁት በዚህ ሁኔታ የሚገኙ ሲሆን፣ እናንተም የጠለቀ የእምነት ልምምድ እንዲኖራችሁ ስትጸልዩ የቆያችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ የሱስ ‹‹ደስታችሁ እንዲፈጸም/ ሙላት እንዲኖረው›› (ዮሐንስ 15፡11) የሚመኝ ሲሆን፣ በዘላለም ሕይወት ጽኑ ተስፋ እንድታርፉ ይጋብዛችኋል፡፡

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

***አሁንም ሥጋውያን ነን፤ ግን ተስፋ አለን***

‹‹እኔም ወንድሞች ሆይ፤ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፣ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም፡፡ ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም፡፡ ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?" (1 ቆሮንቶስ 3፡1-3)

*ውድ ጌታ ሆይ፤ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ‹‹አሁንም›› የሚለውን ቃል አካትተህ በዚህ ሁኔታ መቀጠል እንደሌለብን እንዲያሳስበን ስላደረግህ እናመሰግንሃለን፡፡ ዛሬ እንድትለውጠን እንፈልጋለን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ስንመላለስ የቅናት፣ የጥል፣ እና የመለያየት ሕይወታችን ስለሚፈወስ እናመሰግንሃለን፡፡*

**ልመና የምናቀርበው ከሥጋዊ ፍላጎቶች ተነስተን ነው?**

‹‹…አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ ትለምናላችሁ፤ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም፡፡›› (ያዕቆብ 4፡2)

*አባት ሆይ፤ ስለማንለምን ወይም ደግሞ ከእራስ ወዳድነት በመነጨ ሰብአዊ መነሻ ሀሳቦች ስለምንለምን በመንፈሳዊ ድህነት እንገኛለን፡፡ እባክህ ጸሎቶቻችንን ቀይርልን፤ በመንፈስ ቅዱስም ምራን፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-** በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

## 6ኛ ቀን

### እግዚአብሔር ላለብን ትግል ያቀረበው መፍትሔ

‹‹… በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል፡፡›› (ሉቃስ 9፡23፣24)

### ዘላቂነት ያለው ተሀድሶ ሁለት ምስጢራት

‹‹መንፈሳዊ ክርስቲያን›› መሆን ለሚፈልጉ ‹‹ሥጋዊ ክርስቲያኖች›› ክርስቶስ የሱስ መፍትሔ አቅርቧል፡፡ ‹‹በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ፡፡ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ካልሆነ በቀር ብቻውን ፍሬ ሊያፈራ አይችልም፤ እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ ልታፈሩ አትችሉም፡፡›› (ዮሐንስ 15፡4 አ.መ.ት) በሌላ አባባል ‹‹በእኔ ውስጥ ሁኑ›› ማለት ነው፡፡ ግን እንዴት?

ኤለን ኋይት በክርስቶስ መኖር ምን ማለት እንደሆነ እንዲህ ገልጻለች፡-

- ‹‹በቀጣይነት **የእሱን መንፈስ መቀበል››** እና
- ‹‹ለእሱ አገልግሎት **እራስን ሳይቆጥቡ አሳልፎ መስጠት››** (The Desire of Ages, p. 676)

ይህ ባለ ሁለት ክፍል መፍትሔ ወደ ተሃድሶ ብቻ ሳይሆን፣ ደስታ ወደ ተሞላ የክርስትና ሕይወትም የሚያደርስ ነው፡፡

እንዴት? የሱስ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን፣ ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ፡፡›› (ዮሐንስ 15፡11) እነዚህን ሁለት እርምጃዎች በመውሰድ ‹‹ክርስቶስ በእናንተ›› የተባለውን እንለማመዳለን፤ በሌላ አባባል በየእለት ሕይወታችን የእሱ መገኘት ይኖራል፡፡ የክብሩ ተስፋ ተካፋዮች እንሆናለን ማለት ነው፡፡ (ቆላስይስ 1፡27)

**ወሳኙ ነጥብ፡-** እኛ ማድረግ የሚገባን የመንፈስ ቅዱስን መታደል በእምነት መቀበል እና ያለንን እና የሆንነውን ሁሉ በየቀኑ ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት ነው፡፡ ያኔ እሱ ሐሴት እንዲኖረን ያደርጋል!

በ1ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ልመና ማቅረብ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተነጋግረናል፤ በ3ኛው ቀንም እራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፎ የመስጠት አስፈላጊነትን አይተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ እነዚህን እርምጃዎች በተለየ መልክ እናያለን፤ የተለየ ትኩረታችንም መለመን እና እራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን መስጠት የሚገባን በየእለቱ መሆኑ ላይ ነው፡፡

**መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በየእለቱ ልመና ማቅረብ የሚያስፈልገን ለምንድን ነው?**

ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ የኃይል ጥቃት ፈጻሚ ሰው ሕይወቱን ለክርስቶስ ለመስጠት በቅቶ ነበር፡፡ በሙሉ ልቡ፣ በሰዎች ላይ በሐሰት መመስከሩን፣ ስርቆቱን እና ሌሎች ወንጀሎቹን በመናዘዙ ታላቅ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነትን ተለማምዶ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሕይወቱን ፍጹም ለወጠለት፡፡

በዚህ ተመስጬ፣ እንዲህ በማለት አሰብሁ፡- ‹‹በብዙ መንገዶች ሲታይ፣ በጥሩ ይዞታ የምገኝ ነኝ፤ ነገር ግን እንደ እሱ ያለ ልምምድ አላገኘሁም፡፡›› ስለዚህ እንደዚህ ብዬ ጸለይሁ፡፡ ‹‹ጌታ ሆይ፤ የማውቃቸውን እና ገና አንተ ያልገለጥህልኝን ሐጢአቶቼን መናዘዝ እፈልጋለሁ፡፡ በተጨማሪም፣ በየእለቱ አንድ ሰዓት ቀድሜ በመነሳት መጽሐፍ ቅዱስን እያነበብሁ እጸልያለሁ፡፡ እናም በእኔም ሕይወት ጣልቃ ትገባ እንደሆነ አያለሁ፡፡

እግዚአብሔር ይመስገን፤ በእውነትም እግዚአብሔር በሕይወቴ ጣልቃ ገባ! ይህ ሊሆን የቻለው ማልጄ መነሳቴ ተቆጥሮልኝ ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ እኔን በሚደርስበት ሁኔታ ውስጥ እራሴን በመክተቴ ነበር፡፡ የሱስ በየእለቱ በመንፈስ ቅዱስ እንደ አዲስ መጠመቅ አስፈልጎት የነበረ ከሆነ፣ ለእኛማ ይህ ኃይል ምንኛ የበለጠ ያስፈልገን? ጳውሎስ ስለ የውስጡ ሰው የሚጽፍ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ሰዎች ‹‹በመንፈሱ በውስጥ [ሰውነታቸው] በኃይል [እንዲጠነክሩ] ጸልዮአል (2 ቆሮንቶስ 4፡16 እና ኤፌሶን 3፡16)፡፡ ኤለን ኋ ይትም ይህንን የተሰፋ ቃል አቀብላለች፡- ‹‹ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም ስጦታዎች ለመስጠት ፈቃደኛ ከሚሆኑት በላይ፣ ጌታ ለሚያገለግሉት መንፈስ ቅዱስን ለመስጠት ይበልጥ ፈቃደኛ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሠራተኛ በየእለቱ በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅ እንዲችል፣ ወደ እግዚአብሔር ልመናውን ማቅረብ ይገባዋል››፡፡ (The Acts of the Apostles, p. 50) የውስጡ ሰው በየእለቱ እንክብካቤ ማግኘት ይፈልጋል፡፡

በየእለቱ እራሳችንን ለየሱስ አሳልፈን መስጠት የሚያስፈልገን ለምንድን ነው? የሱስ ደቀ መዛሙርቱ ደቀ መዝሙርነት መሥዋዕትነት የሚያስከፍል መሆኑን እንዲረዱ ብሎ እንዲህ አላቸው፡- ‹‹...በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡›› (ሉቃስ 9፡23) እራስን መካድ ማለት የሱስ ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር በየእለቱ ፈቃዳችንን ለእሱ መስጠት ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ ሁኔታውን ‹‹ዕለት ዕለት እሞታለሁ›› በማለት ገልጾታል፡፡ (1ቆሮንቶስ 15፡31)

‹‹ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ [ ነኝ ]›› የሚለውን እውነታ በመዘንጋት፣ እራስን አሳልፎ መስጠትን እንገፋለን፡፡ (2 ቆሮንቶስ 12፡10) ሕይወትን ያገኘነው ስንወለድ ቢሆንም እንኳ፣ በጤንነት ለመጠበቅ በየእለቱ መመገብ እንቀጥላለን፡፡ ዳግም ስንወለድም፣ መንፈሳዊ ሕይወት እናገኛለን፤ ሆኖም በየእለቱ መንፈሳዊ ምግብ ማግኘት ያስፈልገናል፤ አለበለዚያ እንሞታለን፡፡ ልክ አካላዊ ምግብን አንዴ አስቀድመን በልተን ማቆም እንደማንችል ሁሉ፣ ለነገ ዛሬ እራሳችንን ለክርስቶስ አሳልፈን መስጠት አንችልም፡፡ ኤለን ኋይት እንዲህ ጽፋለች፡- ‹‹ምንም እንኳ ድነትን ባገኘንበት የመጀመሪያ ወቅት እራሳችንን ሙሉ በሙሉ ቀድሰን የሰጠን ቢሆን፣ በየእለቱ ካልታደሰ፣ ምንም አይጠቅመንም፡፡›› (Our Father Cares, p. 144)

**እንዴት መጀመር እንደሚገባ**

በየእለቱ መንፈስ ቅዱስን የመቀበያ እና ለየሱስ እራስን አሳልፎ የመስጫ ምርጡ እና ብቸኛው መንገድ በየእለቱ የግል አምልኮ ማካሄድ ነው፡፡ በየእለቱ እግዚአብሔርን ምርጫችን ካላደረግን በቀር፣ የምንገባቸው ቃል ኪዳኖች እና በጎ ሀሳቦቻችን በሙሉ ‹‹የአሸዋ ገመድ›› ሆነው የሚቀሩ ናቸው:: (Steps to Christ, p. 47) ታዲያ የቀናችሁን ምርጥ ጊዜ ለእሱ ለማጋራት የተሰጠ ውሳኔ ታደርጋላችሁ?

*‹‹ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡››* (*ማቴዎስ* 6፡33)

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

**በምርጡ ግንኙነት ዝለቁ**

‹‹በእኔ ኑሩ፤ እኔም በእናንተ፡፡ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፣ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም፡፡ ... በእኔ ብትኖሩ፣ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፣ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል፡፡›› (ዮሐንስ 15፡4፣7)

*ጌታ ሆይ፤ በየእለቱ እራሳችንን ለአንተ አሳልፈን በመስጠት በአንተ ላይ ያለን መታመን የሚያድግበትን ዕድል ስለሰጠኸን እናመሰግንሃለን፡፡ መንፈስ ቅዱስን በበለጠ እንድናውቅ ምራን፡፡  የአንተ መሻቶች የእኛም መሻቶች ይሁኑልን፡፡*

**በየእለቱ በምርጡ ግንኙነት ዝለቁ**

**‹‹ ...** በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡›› (ሉቃስ 9፡23)

*‹‹ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡ ››* (*ማቴዎስ* 6፡33)

*ውድ ጌታ ሆይ፤ በሁሉም ነገር አንተን ማስቀደምን አስተምረን፡፡ እያንዳንዱን ቀን እንዴት ከአንተ ጋር እንደምንጀምር አሳየን፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-**  በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-**  በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-**  በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

## 7ኛ ቀን

**በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች መሠረት መጸለይ**

ለምኑ፤ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፤ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፤ ይከፈትላችሁማል፡፡›› (ማቴዎስ 7፡7)

**የማይቻሉ ድሎች የሚቻሉ ይሆናሉ**

የሱስ የተቤዥን ‹‹የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል›› ነው (ገላትያ 3፡14)፡፡ ታዲያ እሱ በሰጠው ተስፋ እምነትን የምናዳብረው እንዴት ነው? በመንፈስ ቅዱስ እንደምንሞላ እርግጠኛ በመሆን መጸለይ የምንችለው እንዴት ነው? በልብ መነቃቃት አማካይነት ወደ እውነተኛ የክርስትና ሕይወት ብስለት የሚደረሰው እንዴት ነው?

‹‹በተስፋ ቃሎች መሠረት መጸለይ›› ስለሚባለው የግል የጽሞና ጊዜ አካሄድ ከሰማሁ ብዙ ዓመታት ሆነዋል፤ ግን ለረጅም ጊዜ ሳልተገብረው ቆይቼ ነበር፡፡ ኋላ ላይ ግን፣ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች መሠረት መጸለይ ይዤ፣ የሚገኙበትን በረከቶች ሳይ፣ ልምምዱን ለሰዎች ማካፈል ፈለግሁ፡፡ እናም ከብዙ ዓመታት በፊት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ እንዴት ክርስትናን በተግባር የመለማመጃ ቁልፍ እንደሆነ የሚገልጽ ምዕራፍ የተካተተበት ‹‹ወደ የግል ሕይወት መነቃቃት የሚያደርሱ እርምጃዎች›› የተሰኘ መጽሐፍ ለመድረስ በቃሁ፡፡ አንዳንድ የመጽሐፉ አንባቢዎች ከላኳቸው ምስክርነቶች መካከል የሚከተሉት ሁለቱ ይገኛሉ፡-

‹‹አንተ እንደገለጽኸው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች መሠረት መጸለይን በተመለከተ ያለ አዲስ የጸሎት እውቀት አገኛለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ ታዲያ አሁን በዚህ ሳቢያ መቼም ይሆናሉ ብዬ አስቤያቸው የማላውቀውን ድሎች እግዚአብሔር የሰጠኝ ሆኛለሁ፡፡››

‹‹በተስፋ ቃሎች መሠረት መጸለይን ከተማርሁ ወዲህ ሕይወቴ ተቀይሯል፡፡ .... ባለቤቴ ሕይወቴ ሙሉ ለሙሉ እንደተቀየረ ተገንዝባለች፡፡ እኔም በእራሴ ተደንቄያለሁ፡፡››

**እናንተም ሞክሩት**

በተስፋ ቃሎች መሠረት የሚጸለየው እንዴት ነው? አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃልን ወይም ትእዛዝን መርጠን የዚያን የተስፋ ቃል ወይም ትእዛዝ ቃሎች በመጠቀም ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፡፡ እሱ ቃል እንደገባው እንደሚያደርግ እንታመንበታለን፡፡ በምንጸልየው ጸሎት እንዲመራን እና በቃሉ አማካይነት እንዲናገረን እንፈቅድለታለን፡፡ ማንኛውም ሰው አንዳንድ ጊዜ እንደሚሆንበት ጥርጥር ቢገባን፣ ወደ የተስፋ ቃሎቹ በማመላከት፣ እግዚብሔር ለግላችን የሰጠን መተማመኛዎች መሆናቸውን በእምነት እንቀበላለን፡፡ ልባችን እና ጸሎቶቻችን በእግዚአብሔር ቃል እንዲሞሉ ስናደርግ፣ እምነታችን የሚጠናከር ከመሆኑም ባሻገር፣ እስከ አሁን ሆኖ በማያውቀው መንገድ እና ብልጫ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማወቅ እንበቃለን፡፡ ኤለን ኋይት እንዲህ ጽፋለች፡- ‹‹ከእግዚአብሔር ቃል የተስፋ ቃሎቹን ለመደምሰስ መጣር፣ ከሰማይ ጸሀይን ለመደምሰስ እንደመጣር ነው፡፡.... እግዘአብሔር በቃሉ የተስፋ ቃሎቹን ያኖረው በእሱ ወደማመን እንዲያደርሱን ነው፡፡ በእነዚህ የተስፋ ቃሎች አማካይነት የዘላለም ምስጢራት መጋረጃዎችን ይገልጥልናል፡፡›› (My Life Today, p. 338)

መጽሐፍ ቅዱስ ለምንጸልያቸው ጸሎቶች ግልጽ ምሪት ይሰጠናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ልመናዎቻችንን በየሱስ ስም ማቅረብ እንዳለብን ተነግሮናል፡- ‹‹ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ፡፡›› (ዮሐንስ 14፡14) ‹‹በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል፡፡›› (1ዮሐንስ 5፡14፣15) እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚገልጥልን በመጽሐፍ ቅዱስ ባሉት ትእዛዛት እና የተስፋ ቃሎች ነው፤ እኛም የተስፋ ቃሎቹን እንደሚፈጽም ልንታመንበት እንችላለን፡፡ ቁጥር 15 እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡- ‹‹ የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን፡፡››

ይህ ምን ማለት ነው? ስለ አንድ ጉዳይ እየጸለይን ያለነው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት መሆኑን ካወቅን፣ በዚያው ቅፅበት ጸሎታችንን እየመለሰልን መሆኑን እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ ውጤቱ ገና በገሃድ ላይታየን ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜም በስሜታችን ላይታወቀን ይችላል፡፡ ጸሎቶቻችን የሚመለሱት ግን በእምነት እንጂ በስሜቶቻችን አይደለም፡፡ ስሜቶቻችን በኋላ ነው ተከትለው የሚመጡት፤ በወቅቱ ማድረግ የሚገባ ግን የተስፋ ቃሉን መታመን ነው፡፡

ለምሳሌ ያህል በአልኮል እና በኒኮቲን ሱስ ለተያዙ ሰዎች አብሬያቸው ስጸልይ የተማርኩትን ልንገራችሁ፡፡ አርነት ለመውጣት በሚጸልዩበት ወቅት ምንም ነገር ላይሰማቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን ማድረግ ያለባቸው አርነቱን በእምነት መቀበል ነው፡፡ ምናልባት ግን ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ለመጠጥ እና ለሲጋራ የነበራቸው የቀድሞ ኃይለኛ ፍላጎት እንደተወገደላቸው ልብ ሊሉ ይችላሉ፡፡ በዚያ ጊዜ በጸሎታቸው የለመኑትን አርነት በተጨባጭ አግኝተዋል ማለት ነው፡፡

ኤለን ኋይትም የተስፋ ቃሎችን ይዞ መጸለይን በተመለከተ ያቀረበችው ግንዛቤ አለ፡- ‹‹… እግዚአብሔር ለስሙ ክብር ይሆን ዘንድ እጅግ ከፍ ያለ ልመና ወደ እሱ ሲያቀርቡ በጣም ይደሰታል፡፡ በተስፋ ቃሎቹ እምነት ካላቸው፣ ታላላቅ የጸሎት መልሶችን እንደሚያገኙ መጠበቅ ይችላሉ፡፡›› (The Desire of Ages, p. 668) ‹‹መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ተማፀኑ፡፡ እግዚአብሔር ከሰጠው እያንዳንዱ የተስፋ ቃል ጀርባ ይቆማል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በእጃችሁ ይዛችሁ እንዲህ በሉት፡- ‹እንዳልከው አድርጌያለሁ፤ ‹ለምኑ፣ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፤ ይከፈትላችሁማል› የሚለው የተስፋ ቃልህን ይዤ ነው በፊትህ በጸሎት የቀረብሁት› (ማቴዎስ 7፡7)፡፡›› (Christ's Object Lessons, p. 147)

የሱስ እንዲህ የሚል የተስፋ ቃል ሰጥቷል፡- ‹‹ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፤ ይሆንላችሁማል፡፡›› (ማርቆስ 11፡24) በየእለቱ በተስፋ ቃሎቹ መሠረት እየጸለያችሁ ነው? በእሱ ስም እና እንደ ፈቃዱ ስንጸልይ መላው ሰማይ ይንቀሳቀሳል!

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

**እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ሊሰጠን እየተጠባበቀ ነው**

‹‹እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?›› (ሉቃስ 11፡13)

‹‹ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና፡፡›› (ዮሐንስ 7፡39)

‹‹እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው፡፡›› (የሐዋ. 5፡32)

*አባት ሆይ፣ አንተን ለሚለምኑ፣ በአንተ ለሚያምኑ፣ ደግሞም አንተን ለሚታዘዙ መንፈስ ቅዱስን እንደምትሰጥ አንብበናል፡፡ ይህ መሻታችን ነው፡፡ እባክህ በሕይወታችን ይህንን አከናውንልን፤ በእራሳችን ልናደርገው አንችልምና፡፡ ልባችንን በፍቅርህ ስለምታረሰርስ እናመሰግንሃለን፡፡*

**በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ ይጋብዘናል**

‹‹መንፈስ ይሙላባችሁ…›› ወይም ‹‹በቀጣይነት እና በመደጋገም በመንፈስ ቅዱስ እንደገና ለመሞላት እራሳችሁን ዘርጉ፡፡ (ኤፌሶን 5፡18)

*ውድ አባት ሆይ፤ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድልን በቀጣይነት እና በመደጋገም መጸለይን አስተምረን፡፡ እንደ ሞኞቹ ቆነጃጅት የመንፈስ ቅዱስ ጉድለት እንዲኖረን አንፈልግም፡፡ በቃልህ ባለው ጥበብ ሙላን፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

***ምሪት፡-*** በአሁኑ ወቅት በምትገኙባቸው ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

***ቤተ* ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**የአካባቢያችሁ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

**8ኛ ቀን**

**በክርስቶስ ታዛዥ መሆን**

‹‹ስለዚህ ማንም በክርስቶ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡›› 2 ቆሮንቶስ 5፡17

***የእምነት* እርምጃዎች**

የሱስ በቃና በነበረው ሠርግ የፈጸመውን ተአምር ታስታውሳላችሁ? የየሱስ እናት ማርያም አገልጋዮቹን ‹‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ›› ነበር ያለቻቸው (ዮሐንስ 2፡5)፡፡ ማርያም ይህንን በማለት አገልጋዮቹ በየሱስ እንዲተማመኑ አደረገች፡፡ የሱስ የውኃ ጋኖቹን በውኃ እንዲሞሉ በነገራቸው ጊዜ፣ በትክክል እሱ እንዳላቸው ነበር ያደረጉት፡፡ ከዚያም የሱስ ‹‹አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፡፡›› (ቁጥር 8) በዚህ ጊዜም፣ ምንም እንኳ እንዲያደርጉ የነገራቸው ነገር ግር የሚል የነበረ ቢሆን፣ በድጋሚ እንዳላቸው ነበር ያደረጉት፤ ወዲውኑም፣ ተአምራት ሲፈጸም ማየታቸውን ተገነዘቡ፡፡ እስቲ ደረጃዎቹን እንደገና አንድ በአንድ ተመልከቱ፡-

- ማርያም ለአገልጋዮቹ በሰጠችው መመሪያ **በየሱስ መታመንን** እንዲያዳብሩ አደረገች፡፡
- አገልጋዮቹ የሱስ ያላቸውን በቀጥታ በማድረግ መታመናቸውን እና ፈቃደኝነታቸውን ገለጹ፡፡ በሌላ አባባል፣ ተአምሩ እንዲፈጸም የሚያስችሉ **የመንደርደሪያ እርምጃዎች** ነበር የወሰዱት፡፡
- **ከዚያም የሱስ ብቻውን ተአምሩን ፈጸመ፡፡**

አገልገዮቹ ውኃው ወደ ወይን እንዲቀየር ያደረጉት ነገር አልነበረም፤ ግን የመንደርደሪያ እርምጃዎቹን ባይወስዱ ኖሮ፣ ተአመሩ ይፈጸም ነበር? የእምነት መታዘዝ እንዲህ ነው፡- እኛ የሱስን እንመርጣለን፤ ፈቃዳችንን ለእሱ እናስረክባለን፤ ከዚያም በእምነት የመታዘዝ እርምጃዎች እንወስዳለን፤ ተአምራቱን የሚፈጽመው ግን የሱስ ብቻውን ነው፡፡

**አሠራሩ**

ሐዋርያው ጳውሎስ በሆነ ዓላማ አንድ ምስጢር በሕይወታችን መገለጡን እና ይኸውም ዓላማ ከእምነት የሚመጣ መታዘዝን ለማስገኘት እንደሆነ አስታውቋል (ሮሜ 16፡25-27)፡፡ ይህ ምስጢር ምንድን ነው? በቆላስይስ 1፡27 ምስጢሩ ‹‹ክርስቶስ በእኛ›› መሆኑ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ ታዲያ በክርስቶስ በመሆን የእምነት መታዘዝ ሲተገበር የሚከተለው ውጤት ምንድን

ነው? ‹‹ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡›› (2 ቆሮንቶስ 5፡17) ክርስቶስ በእኛ በመኖሩ እና በመሥራቱ አዲስ ሕይወት አግኝተናል፡፡ አዲስ ፍጥረት ሆነናል!

‹‹ክርስቶስ በእኛ›› ሲኖር ለሕጉ ያለን አመለካከት ይቀየራል፡፡ ‹‹…ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም፡፡›› (1ዮሐንስ 5፡3) ‹‹ሸክሜም ቀሊል ነውና፡፡›› (ማቴዎስ 11፡30) ‹‹እጅግም በወደድኋቸው በትእዛዛትህ ደስ ይለኛል፡፡›› ‹‹ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ [ይሻለኛልና]፡፡›› ‹‹ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤›› (መዝሙር 119፤47፣ 72፤103) ‹‹ሕግህን ለሚወድዱ ብዙ ሰላም ነው፤ ዕንቅፋትም የለባቸውም ፡፡›› (መዝሙር 119፤165)የእምነት መታዘዝ ምርጥ ነገር ነው፤ ይኸውም፣ እግዚአብሔር በፍቅሩ የሰጠን ምርጥ የሆኑ መመሪያዎችን ብቻ በመሆኑ ነው፡፡

መታዘዝ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ድነትን ለማግኘት ብቁ የሚያደርገን አይደለም፤ ደግሞም በእኛ መልካምነት የሚሆን አይደለም፡፡ ኤለን ኋይት እንዲህ ብላለች፡- ‹‹ሕግን በመጠበቅ እራሱ በሚሠራቸው ሥራዎች ወደ ሰማይ ለመድረስ የሚጥር ሰው የማይቻል ነገርን እየሞከረ ነው ያለው፡፡ ሰው ያለ መታዘዝ መዳን አይችልም፤ ሆኖም የሚሠራቸውን ሥራዎች የሚሠራው በእራሱ ሊሆን አይገባም፤ ክርስቶስ ነው ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በሰው ውስጥ መፈጸም የተገባው፡፡›› (Faith and Works, p. 94) ሦስት ትኩረት ሊሰጥባቸው የተገባቸው ነጥቦች አሉ፡-

- በገዛ እራስ ሥራ ወደ ሰማይ መድረስ አይቻልም፡፡ በእራስ ብቃት ከእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማግኘት መጣር ከንቱ ነው፡፡
- የሆነ ሆኖ፣ መታዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር ሕይወት አስፈላጊ እና ሊተው የማይቻል ክፍል ነው፤ ይኸውም የየሱስ ተከታዮች የተጠሩት ከፈቃዱ ጋር በተሰማማ አኗኗር እንዲኖሩ በመሆኑ ነው፡፡
- መታዘዝ በገዛ እራሳችን ሥራ የሚከሰት ሳይሆን፣ ክርስቶስ በእኛ የሚያከናውነው ተአምር ሊሆን የተገባው ነው፡፡

**የእኛ ድርሻ ምንድን ነው?**

በድጋሚ ማስታወስ የሚገባን በእራሳችን ምንም ነገር ማድረግ እንደማንችል እና እግዚአብሔር ለሰበአዊ ፍጡራን የሰጠውን ነፃ ፈቃድ አክብሮ የመምረጥ ዕድል እንደሚሰጠን ነው፡፡ ኤለን ኋይት እንደገለጸችው ‹‹ጌታ ያቀደው መለኮታዊ ኃይል ከሰብአዊ ጥረት ጋር እንዲተባበር ነው›› (Ye Shall Receive Power, p.10) ይህ ምን ማለት ነው?

- **እንታመናለን፡፡** ‹‹መፈለግንም ማድረግንም›› በእኛ በሚፈጽመው በየሱስ ያለንን መታመን ማዳበርን እንመርጣለን (ፊልጵስዩስ 2፡13)፡፡ እሱም በውስጣችን ፈቃደኝነትን በማሳደር ማድረግ የሚገባንን ያሳየናል፡፡
- **እንወስናለን፡፡** የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ መምረጥ አለብን፡፡ እግዚአብሔር፣ ግለሰብነታችንን እና ነፃ ምርጫችንን ሙሉ በሙሉ በማክበር በሕይወታችን ጣልቃ የሚገባው ውሳኔ ስናደርግ ብቻ ነው፡፡ እናም ውሳኔውን እስክናደርግ ይጠብቃል፡፡
- **የመንደርደሪያ እርምጃዎች እንወስዳለን፡፡** ትላልቅም ሆኑ ትናንሽ፣ የመታዘዝ እርምጃዎች በመውሰድ ውሳኔያችንን እንገልጻለን፡፡
- ወሳኙን የድነት ሥራ የሚሠራው **እግዚአብሔር ብቻውን** ነው፡፡

የመታመን፣ የመወሰን፣ እና የመንደርደሪያ እርምጃዎች የመውሰድ ድርሻችንን የምንወጣው በእግዚአብሔር ብርታት ብቻ፣ ይኸውም የሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጣችን ሲኖር ብቻ፣ መሆኑን እናስታውስ፡፡ ይህም፣ መታዘዝን ሐሴት ያደርግልናል፡፡

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

**መታዘዝ የእግዚአብሔርን ፍቅር በሙላት መለማመድ ያስችለናል**

‹‹ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ፡፡›› (ዮሐንስ 14፡21)

*ኣባት ሆይ፤ ማግኘት የመንችለውን ምረጥ ሕይወት ስላሳየኸን እናመሰግንሃለን፡፡ ሕግህን እና ፍቅርህን ስለመግፋታችን ይቅር በለን፡፡ በአንተ ሙሉ በሙሉ ወደ መታመን እና በሙሉ ልባችን እራሳችንን ለአንተ አሳልፈን ወደ መስጠት ምራን፡፡*

**እግዚአብሔር ታዛዥ ልብ እንዲኖረን እንዲረዳን እሱን በመማፀናችን ይደሰታል**

‹‹ስለዚህም ... ለባርያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው፤ ... ነገሩ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው፡፡... እንደ ቃልህ አድርጌልሃለሁ፤...›› 1 ነገሥት 3፡9፣ 10፣ 12

*ጌታ ሆይ፤ እባክህ ታዛዥ ልብ ስጠን፤ በአመራርህ እና በመርኀዎችህ ሙሉ በሙሉ እንድንታመን እርዳን፤ ይህም በማናስተውላቸው ጊዜያት ሳይቀር ይሁንልን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት መታዘዝን እንደ ሸክም ሳይሆን እንደ ደስታ ማየትን አስተምረን፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-** በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤት ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

**9ኛ ቀን**

**እኔ ለእግዚአብሔር እየጣርሁ ነው? ወይስ እሱ ነው በእኔ እየሠራ ያለው?**

‹‹ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤...›› ገላትያ 2፡20

***መልካም ሥራ ለመሥራት የተፈጠርን ነን***

ዞልት የሚባለው የኦስትሪያ የነገረ መለኮት ተማሪ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ የገባበት ወቅት ነበር፡፡ በኬንያ የወንጌል ጥረት ለማካሄድ ተጋብዞ ነበር፤ ግን በመጀመሪያው ሳምንት እያንዳንዱ ምሽት በየቀኑ የሚገኙት 30 ተጋባዦች ብቻ ነበሩ፡፡ ተስፋ ያደረገው ከዚያ እጅግ የሚበዙ ሰዎች እንደሚመጡ ነበር፡፡ ተስፋ መቁረጥ አድሮበት የክፍሉን በር ቆልፎ የ4 ሰዓታት የጸሎት

ቆይታ አሳለፈ፡፡ የተስፋ መቁረጡን ሁኔታዎች በሙሉ ለእግዚአብሔር በግልጽ በመንገር፣ መላ ማንነቱን ለእሱ አሳልፎ በመስጠት መጠበቅ ያዘ፡፡ እግዚአብሔር እንደሰማው እርግጠኛ የነበረ ቢሆንም፣ በነበሩት የፍርሃት እና የጥርጥር ስሜቶች መታወኩን ቀጥሎ ነበር፡፡ ከዚያ የምሽቱ ስብሰባ ደረሰ፡፡ 600 ሰዎች ነበር የተገኙት! ኋላ ላይ 700፣ በኋላም በእግዚአብሔር ጸጋ 39 ሰዎች ለመጠመቅ በቁ፡፡

ለእግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን ለማከናወን በምንጥርበት ጊዜ የምንጋፈጠው ወሳኝ ጥያቄ እንዲህ ነው፡- ‹‹በሰብአዊ ችሎታዎቼ ለእግዚአብሔር ለመሥራት እየጣርሁ ነው? ወይስ እግዚአብሔር ነው በመለኮታዊ ችሎታዎቹ በእኔ እየሠራ ያለው?››፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ብርቱው እግዚአብሔር በደካማ ሰብአዊ ፍጡራን የመሥራቱን ምስጢር እንዲህ ገልጿል፡፡ ‹‹እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፡፡›› (ኤፌሶን 2፡10) ይህ ጥቅስ የሚያመላክተው ወደ ሁለት ዓይነት ‹‹ሥራዎች›› ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ እግዚአብሔር ‹‹በክርስቶስ የሱስ ፈጠረን››፤ ይህም በክርስቶስ የሰጠን አዲስ ሕይወት ነው፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር በእኛ ሁለተኛ ሥራ ይሠራል፣ ይኸውም አስቀድሞ እንድንሠራቸው ያዘጋጀልንን ‹‹መልካም ሥራዎች›› ነው፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር እነዚህን ሥራዎች በእኛ መሥራት እንዲችል በምን ዓይነት አኗኗር መኖር ይገባናል?

- **በመንፈስ በመመላለስ፡-** ‹‹መንፈስ ቅዱስን እስከሚቀበሉ፣ እግዚአብሔር በእነሱ መሥራት የሚችለውን መገንዘብ አይቻላቸውም፡፡›› (Ye Shall Receive Power, p . 286)
- **እራስን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ አሳልፎ በመስጠት መመላለስ፡-** ሙሉ በሙሉ እራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ የሚሰጥ ሰው በመለኮት እጅ ይመራል፡፡ … ከመለኮት ጥበብ የሚያገኛቸውን ትምህርቶች እጅግ አክብሮ እና ወዶ በመያዙ፣ የተቀደሰ ተልዕኮ አደራ ይሰጠዋል፡፡›› (The Acts of the Apostles, pp. 283, 284)

እግዚአብሔር እንድንሠራቸው ያዘጋጀልንን ሥራዎች ጠንቅቀን ስናከናውን፣ በእምነት ከማደጋችንም ባሻገር፣ መንፈሳዊ እና የአዕምሮ ችሎታዎቻችን ይበለጽጉልናል፡፡ ውድቀቶቻችን እንኳ የከበሩ ትምህርቶች ያስገኙልናል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ማዕከል ያልሆነበት ማንኛውም ሰብአዊ ጥረት እንደማይሳካ ስለምንማርባቸው ነው፡፡ ‹‹ቀጣይነት ባለው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት እና እርዳታ የማይተገበር የቃሉ ስብከት ምንም ጥቅም የማያስገኝ ነው›› (The Desire of Ages, p. 671)

### በኃይል እና በብርታት አይደለም

ልክ እንደ ሰባኪያን፣ የመንፈሳዊ ጽሑፎች ደራስያን በእግዚአብሔር ኃይል መታጠቅ አለባቸው፡- ‹‹ጽሑፍ የሚያዘጋጀው ሰው ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ድነት ያገኘ ከሆነ፣ ያው መንፈስ በአንባቢው ያድራል፡፡… ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ክብር ባልዋለ አኗኗር የማይኖር እና የተሰጠ ሕይወት የሌለው ሰው በሚያዘጋጀው ጽሑፍ ጉድለት መላእክት ያዝናሉ፡፡ እግዚአብሔር እና መንፈሱ በጽሑፉ ባለመኖራቸው፣ መላእክት ገሸሽ ብለው አንባቢውን ሳይመስጡ ይቀራሉ፡፡›› (EGW Letters and Manuscripts, vol. 1, p. 532)

ይህ መርኅ፣ በወንጌል አገልግሎትም፣ በማስተማርም፣ የወንጌል ተጓዳኝ ሥራን በመምራትም፣ ልጅን በማሰልጠንም፣ ወይም በማንኛውም ሌላ ተግባር፣ ባጠቃላይ በሁሉም ተግባሮች እውነት ነው፡፡ ‹‹በሥራው ስኬት የሚያስገኘው ከሰው የሚመነጨው ኃያል ሳይሆን፣ ከሚያገለግለው ሰብአዊ ፍጡር ጋር በመተባበር የሚሠራው የሰማይ ምጡቅ ማስተዋል ኃይል ነው፡፡›› (Christian Service, p. 260)

የናዝሬቱ የሱስ እንኳ በሰብአዊነት ይመላለስ በነበረበት ወቅት በየእለቱ ይደገፍ የነበረው ከሰማይ ጋር በነበረው ተያያዥነት ነው፡፡ ‹‹እኔ በአብ እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ

የሚኖረው አብ እርሱ *ሥራውን ይሠራል›› ነበር ያላቸው ደቀ መዛሙርቱን* (ዮሐንስ 14፡10)፡፡ *ደግሞም ሐዋርያው ጳውሎስን ማየት እንችላለን፡፡ አንድ ሰው እንዲህ በማይታመን ሁኔታ ታላቅ የወንጌል ሥራን መወጣት የቻለው እንዴት ነው?* ‹‹ከክርስቶስ *ጋር* ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን *ሕያው ሆኜ* አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤›› ነበር *ያለው* ጳውሎስ (*ገላትያ* 2፡20)፡፡ *ጳውሎስ* እራሱን በእራሱ *የመምራት* አካሄዱን ትቶ፣ ሕይወቱን እንዲመራለት ለክርስቶስ ፈቀደለት፡፡ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ነገሩን አብራርቷል፡- ‹‹አሕዛብ እንዲታዘዙ፣ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፤ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤...›› (ሮሜ 15፡18፣ 19) ቁልፉ በክርስቶስ *መኖር ነው*፡፡

እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜም እጅግ ድንቅ ነገሮችን መፈጸም ፈቃዱ ነው፡፡ እቅዶቹ ከእኛ ችሎታዎች እጅግ የሚያልፉ ናቸው፡፡ እሱ ለእኛ ያዘጋጀልንን ተግባር መወጣት የምንችለው ቀጣይነት ባለው ጸሎት ከእሱ *ጋር* በመያያዝ ብቻ ነው፡፡ እንዲህ በማለት እየጋበዘን ነው፡- ‹‹... ወደ እኔ ጩኽ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና *ኃይለኛ* ነገርን አሳይሃለሁ፡፡›› (ኤርምያስ 33፡3)

**በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መጸለይ**

**ሰብአዊ ችሎታዎች የሚያስገኙት ሰብአዊ ውጤቶች ብቻ ነው**

‹‹ሙሴም የግብፆችን ጥበብ ሁሉ ተማረ፤ በቃሉና በሥራውም የበረታ ሆነ፡፡... ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም፡፡ ... [እግዚአብሔር] ድንቅና ምልክት እያደረገ አወጣቸው፡፡›› (የሐዋርያት ሥራ 7፡22፣ 25፣ 36)

*የተወደድህ አባት ሆይ፤ ሙሴ በእረኝነ ካሳለፋቸው ዓመታት በኋላ እንዳደረገው፣ እራሳችንን ለአንተ አሳልፈን ወደ መስጠት ምራን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንመላለስ፣ በእኛም ምልክቶችን እና ድንቆችን መፈጸም እንደሚቻልህ እናውቃለን፡፡ ወደምትመራን ለመሄድ ፈቃደኛ እንድንሆን እርዳን፡፡ ስለመለኮታዊ ኃያልህ እናመሰግንሃለን፡፡*

**መልካም ሥራዎች ለመሥራት በክርስቶስ የተፈጠርን ነን**

‹‹እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ እየሱስ ተፈጠርን፡፡›› (ኤፌሶን 2፡10)

*ጌታ ሆይ፤ ለጎረቤቶቻችን መዳን የምትጠቀምብን አድርገን፡፡ ‹‹በሰብአዊ ችሎታዎቼ ለእግዚአብሔር ለመሥራት በመጣር ላይ ነኝ? ወይስ እግዚአብሔር ነው በመለኮታዊ ችሎታዎቹ በእኔ እየሠራ ያለው?›› በሚለው ጥያቄ ላይ የወንጌል ግብ መምታት እንዳለፈ እናውቃለን፡፡ በእራሳችን አንተን ማገልገል እንደማንችል አስተምረን፡፡ በእኛ ለመሥራት ቃል ስለገባህ እናመሰግንሃለን፡፡ እባክህ የእጆቻችንን ሥራ ባርክ፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-** በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

***ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-*** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡

**10ኛ *ቀን***

***በሕብረት ተሃድሶን መሻት***

‹‹…በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር›› ዘካርያስ 4፡6

***ቀጥሎስ?***

***መንፈሳዊ ጉዞን እንደገና ለመጀመር የሚጠቅሙ ሦስት እርምጃዎች***

ከመላው የቤተ ክርስቲያናችሁ ቤተሰብ ጋር የመንፈሳዊ ልምምድ ተሃድሶ ማግኘት ትፈልጋላችሁ? በዚህ ክፍል አንድትሞክሩት የቀረበው እቅድ በጀርመን፣ በስዊዘርላንድ፣ በእንግሊዝ፣ በታጂኪስታን፣ እና በሰሜን አሜሪካ መንፈሳዊ መነቃቃት ያስከተለ ነው፡፡ ዓለማዊ በሚባሉ አገሮች ሳይቀር፣ ሰዎች በቀጣይነት እራሳቸውን ለየሱስ አሳልፈው እየሰጡ የመንፈስ ቅዱስን በረከት ለማግኘት በሚጸልዩበት ማንኛውም ስፍራ መነቃቃት ሊከሰት ይችላል፡፡

በዚህ ዓመት በመላው የቤተ ክርስቲያናችሁ ቤተሰብ ወይም በጸሎት ቡድናችሁ እንዴት መንፈሳዊ ጉዟችሁን ‹‹እንደገና መጀመር›› እንደምትችሉ በተመለከተ ጸልዩ፡፡ እቅድ አውጡ፤ የሌሎች የቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት ሀሳቦችን ተቀበሉ፤ ከዚያም የተሰማማችሁበትን አካሄድ የምትጀምሩበትን ቀን ወሰኑ፡፡ የያዛችኋቸውን ሀሳቦች ለባህላችሁ፣ ለማኅበረሰባችሁ፣ እንዲሁም ለቡድናችሁ ፍላጎቶች ተሰማሚ በሚሆኑበት መንገድ አመቻችታችሁ መጠቀም ይጠቅማችኋል፡፡

ልናካፍላችሁ የወደድነው በሰሜን አሜሪካ የአላባማ ክፍለ ሀገር በዴካቱር የምትገኘውን የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ብቻ ነው፡፡

1. ***እንደገና መጀመር***

   ***የእግዚአብሔርን ቃል እያጠናችሁ፣ እንዲሁም ከቻላችሁ፣ አጫጭር የየእለት የጽሞና ጊዜ ንባቦች የያዘ መጽሐፍን እየተጠቀማችሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ብዙ ሳምንታት ወይም ወራት በጸሎት አሳልፉ፡፡***

   የዴካቱር ቤተ ክርስቲያን አባላት ለተከታታይ የወንጌል ጥረት ስብሰባዎች ባደረጉት ዝግጅት በየሰንበት ጠዋት ለ30 ደቂቃ አንድላይ መጸለይ ያዙ፡፡ የጸሎት ልምምድን፣ ተሃድሶን፣ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ አሠራርን የሚያደፋፍሩ እና የሚያጎለብቱ ፍንጮችን በቤተ ክርስቲያኗ የማስታወቂያ በራሪ ወረቀት ይለቁ ነበር፡፡ ደግሞም በሁለት ሰንበት ምሽቶች መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ የቪዲዮ ሴሚናር አካሂደው ነበር፡፡ ከሴሚናሩም በኋላ፣ መንፈሳዊ ተሃድሶን የሚመለከት ትንሽ መጽሐፍ ለአባላት በማዳረስ፣ በቀጣዮቹ ስድስት ሳምንታት መጽሐፉን እንዲያነቡ አሳሰቧቸው (እነሱ የመረጡት መጽሐፍ *መነቃቃት ወደ ግል ሕይወት መነቃቃት የሚመራ መንገድ* የሚለውን ነበር፡፡ ከሌሎች አማራጮች መካከል ደግሞ *ወደ ክርስቶ የሚመራ መንገድ* የሚለው መጽሐፍ እና ተሃድሶን የሚመለከት ጥሩ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ መጽሐፍ ይካተታሉ)፡፡ ኋላ ላይ የ10 ቀናት የጸሎት ቆይታ በተካሄደበት ወቅት የተሃድሶ እና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ልምምድ ለማግኘት ከመጸለያቸውም ባሻገር፣ የሰንበት የጸሎት እና የውዳሴ በዓል አብረው አሳልፈዋል፡፡

2. **የወዳጅነት እንክብካቤ**

**እያንዳንዳችሁ የቤተ ክርስቲያን አባላት በወንጌል ላልደረሳችኋቸው አምስት ሰዎች የምልጃ ጸሎት መጸለይ ከጀመራችሁ በኋላ፣ በእውነተኝነት እና ቅንነት በተሞላ የዘዴ አቀራረብ ወደ እነሱ ሄዳችሁ ከእነሱ ጋር ጓደኝነት መሥርቱ፡፡ ታዲያ በዚህ ወቅት፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት በአንድነት ጸሎትን ወይም ተሃድሶን የሚመለከት ሌላ መጽሐፍ ማንበብ ከፈለጋችሁ፣ ትችላላችሁ፡፡ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ አብራችሁ መንፈሳዊ ጥናት በማካሄድ፣ እርስ በርስ የመበረታታት እና ወደ ጥልቅ መንፈሳዊ ማስተዋል የምትደርሱበትን ዕድሎች ለማመቻቸት ተነጋገሩ፡፡**

በዚህ ሁለተኛው ደረጃ የዴካቱር ቤተ ክርስቲያን አባላት *40 ቀናት፦ የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ለጌታ ዳግም ምጻት ለመዘጋጀት* የተሰኘውን መጽሐፍ ሁለት ሁለት እየሆኑ ያጠኑ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ለሰዎች ስለ የሱስ የመናገር ሐሴት የተሞላ ፍላጎታቸው እየጨመረ ሄደ፡፡ ደግሞም በመጽሐፉ በቀረበው ሀሳብ መሠረት እያንዳንዳቸው አባላት በወንጌል ላልደረሷቸው አምስት ሰዎች መጸለይ ጀመሩ፡፡ ከዚያም እነዚያን የሚያውቋቸው ሰዎች እና የቀድሞ የቤተ ክርስቲያን አባላት ፈልገው በማግኘት፣ በየጊዜው ከእነሱ ጋር መገናኘት ቀጠሉ፡፡ የዚህም ውጤት ሰዎች መጠመቃቸው፣ እንዲሁም አዳዲስ አባላቱም የጸለዩላቸው ሰዎችም በረከቶችን መቀበላቸው ነበር፡፡

እስቲ እናንተም አስቡበት፦- 10 የቤተ ክርስቲያን አባላት ለአምስት ለአምስት ሰዎች በየእለቱ እየጸለዩ፣ እነዚያን ሰዎች በዚህ መንገድ ቢቀርቡ፣ በወንጌል የሚደረሱት አዳዲስ ሰዎች ቁጥር 50 ይሆናል ማለት ነው፤ ከዚህም ተነስቶ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ 40 ቀናቱ ሲገባደዱ፣ የጸለያችሁላቸውን ሰዎች በተለየ የእንግዶች ሰንበት ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን መጋበዝ ትችላላችሁ፡፡ ቀጥሎም እያንዳንዳቸው አዳዲስ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን የሚካሄዱ የትናንሽ ቡድኖች እንቅስቃሴዎችን እንደየምርጫቸው እንዲቀላቀሉ ጋብዟቸው (ቡድኖቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የጤና ምግብ አዘገጃጀት፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ ወይም የማህበራዊ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ)፡፡ በተጨማሪም፣ በመጪዎቹ የወንጌል ጥሪት ስብሰባዎች እንዲገኙ ልትጋብዟቸው ትችላላችሁ፡፡ ከምትጋብዟቸው ጓደኞቻችሁ ጋር አብራችሁ በመሆንም ስብሰባዎቹን መካፈል እና መልካም አቀባበል እንዳገኙ እንዲሰማቸው ማድረግ እንደሚገባችሁ አስታውሱ፡፡

3. **ማካፈል**

**እያንዳንዳችሁ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስትጸልዩላቸው የቆያችሁ ሰዎችን በወንጌል ጥሪት ስብሰባዎች፣ በትንሽ ቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፣ ወይም በግል በሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲሳተፉ መጋበዝ ትችላላችሁ፡፡ (እየጸለያችሁላቸው የምትጠያየቋቸው ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ለመሳተፍ ገና ዝግጁነት የሌላቸው ከሆነ፣ እንደ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ የጤናማ ምግብ አዘገጃጀት፣ የትርፍ ጊዜ መዝናኛዎች፣ ወይም ማኅበራዊ ጉዳዮች ባለ ዝንባሌያቸው የሆነ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረ ትንሽ ቡድን መርጠው እንዲሳተፉ ጋብዟቸው፡፡)**

የዴካቱር ቤተ ክርስቲያን ተከታታይ የወንጌል ጥሪት ስብሰባዎች ባካሄደችበት ወቅት አባላቱ የተሃድሶ እና ከየሱስ ጋር የጠለቀ ግንኙነት ልምምድ ለማግኘት በቁ፡፡ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ በተጋባዦቹ ልብ ሠርቶ 10 ሰዎች በጥምቀት እራሳቸውን ለየሱስ ሰጡ (ኋላ ላይም 5 ተጨማሪ ሰዎች ተቀላቀሏቸው)፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው በጸሎት ኃይል ነበር! (የዴካቱር ታሪክ የተወሰደው በአንድ ተነባቢ ጽሑፍ በኤሊዳ ሜኔሰስ ከቀረበው ዘገባ ነው፡፡)

**እናንተስ በቤተ ክርስቲያናችሁ ምን ማድረግ ትችላላችሁ?**

ዛሬ አብራችሁ በመጸለይ ለቤተ ክርስቲያናችሁ እቅድ አውጡ፡፡ ‹‹ሰማይ በመላ በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ሲሆን፣ ክርስቶስ የሞተላቸው ሰዎች አስደሳቹን የድነት ዜና እንዲሰሙ እቅድ ከሚቀይሱ ሰዎች ሁሉ ጋር ለመተባበር መላእክት ይጠባበቃሉ፡፡

ድነትን ሊወርሱ ላላቸው ሰዎች አገልግሎት የሚሰጡ መላእክት እያንዳንዳቸውን እውነተኛ ቅዱሳን ‹የምትሠሩት ሥራ አለላችሁ› ይሏቸዋል፡፡ ‹ሂዱና ቆማችሁ የዚህን ሕይወት ቃል ሁሉ ለሕዝብ … ንገሩ…› (የሐዋርያት ሥራ 5፡20)›› (Testimonies for the Church, vol. 6, pp. 433, 434)

እግዚአብሔር ወደ ዓለም የላካችሁ በዚህ የተስፋ ቃል ነው፡- ‹‹እያቀዳችሁት ያለው እቅድ በሠራዊት ኃይልም ሆነ በሰብአዊ ብርታት ስኬት የሚገኝበት አይደለም፤ ይልቁኑ የእኔ መንፈስ ያከናውነዋል እንጂ! ሁሉን ቻይ የሆንሁ እኔ ጌታ እግዚአብሔር ይህንን ቃል ገብቼአለሁ፡፡›› (ዘካርያስ 4፡6 ‹‹ሆፍኑን ፊዮ አለ›› ለተሰኘው የጀርመንኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቀረብ ያለ ትርጉም)

*‹‹ውድ አባት ሆይ፤ ስኬት የሚገኘው በሰብአዊ ጥረት እንዳይደለ ነግረኸናል፡፡ እባክህ ስለ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጉድለታችን ይቅር በለን፡፡ እንደ ሎዶቅያ ለብ ያልን እንዳንሆን መነቃቃትን አስገኝልን፡፡ ስለ እራሳችን እና ስለ ጎረቤቶቻችን ድነት እንድንተጋ አንቃን፡፡ ዘላለማዊ ሐሴትን ልትሰጠን ቃል ስለገባህልን እናመሰግንሃለን፡፡*

**ተጨማሪ የጸሎት ርዕሶች**

**ምስጋና እና ውዳሴ፡-** ስለምታውቋቸው ያገኛችኋቸው በረከቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደግሞም ስለ መልካምነቱ አወድሱት፡፡

**ኑዛዜ፡-** በግላችሁ ሐጢአታችሁን ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ እና ይቅር ስለሚላችሁ እሱን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች ውሰዱ፡፡

**ምሪት፡-** በአሁኑ ወቅት ባሉባችሁ ተግዳሮቶች እና በምትወስዷቸው ውሳኔዎች እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ እሱን ለምኑ፡፡

**ቤተ ክርስቲያናችን፡-** በአገር፣ በአህጉራት፣ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የሚተገበሩትን የቤተ ክርስቲያናችን ጥረቶች እግዚአብሔር እንዲባርክ እሱን ለምኑ፡፡

**በአካባቢያችሁ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጸሎት ርዕሶች፡-** በአሁኑ ወቅት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት፣ ቤተሰቦቻችሁ፣ እና ጎረቤቶቻችሁ ስላሏቸው ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡

**ማዳመጥ እና ምላሽ መስጠት፡-** የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማችሁ፣ በውዳሴ ወይም በዝማሬ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ውሰዱ፡፡